


# ትንሣኤ

[illegible]



"... ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናም የምትጠጣ መሬት ለሚያርሱአትም ደግሞ የሚጠቅሙ አትክልትን የምታበቅል ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለች ።" ዕብ. ፮ ፯

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር ፶፰ ሐምሌ ፲፱፻፸፬ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

“ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ “ትንሣኤ” ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ራደ አስረስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ወርኃ ክረምት | ፪ |
| የቤተ ክርስቲያን ሕይወት | ፫ |
| ቅዱስ ያዕቆብ የጌታችን ወንድም ለምን ተባለ ? | ፬ |
| «አይዞአችሁ አትፍሩ » | ፮ |
| ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ | ፯ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፱ |
| ቅዱስ ታዴዎስ ሐዋርያ | ፲ |
| ዜና ሊቃውንት | ፲፪ |
| ትምህርተ ግእዝ | ፲፬ |
| የወጣቶች ምስክርነት | ፲፮ |
| «በእኔ ላይ የፈላጋችሁትን አድርጉ » | ፲፯ |
| ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተ ሰብእ | ፲፰ |
| አራት ዐይናው ዓሣ | ፳ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፳፩ |
| ክርስቲያናዊ ጋብቻ | ፳፫ |

# ደብዳቤዎች

**ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ**
**አዲስ አበባ**

ከሁሉ በማስቀደም በልዑል እግዚአብሔር ስም ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከሰላምታዬ በኋላ ግን ከዚህ በታች ያቀረብኳቸውን ጥያቄዎች እንድታብራራልኝ እጠይቃለሁ ።

በቁጥር ፶፪ ትንሣኤ መጽሔት “ጥምቀት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት’ በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ ለእኔ እንደተሰማኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ከሌላው ጋር ለማዛመድና ለማቀራረብ የተደረገ ሙከራና ይሉኝታ ያለበት መስሎ ስለታየኝ በቅድሚያ ቅሬታዬን እገልጻለሁ ።

ስለዚህ ፩ኛ “ጥምቀት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ” በሚል ርእስ እንዲጻፍ ለምን ተፈለገ ? ትምህርት ለመስጠት ከተፈለገ ልዩነቱ በሚገባ ለምን አልተገለጸም ?

፪ኛ/ አንድነትና ሦስትነትን እንዲሁም አንዲት ጥምቀት አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብለው ማመናቸው እንዴት ነው? እንዲህ ካመኑ ለምን ተለያዩ ?

፫ኛ/ በመጨረሻም የዓምዱ አዘጋጅ ማጠቃለያ ሐሳብ ሲሰጡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወንድ በ፵ ሴት በ፹ ቀን የሚጠመቁበት በቂና ትክክለኛ ምክንያት ያለው ሲሆን እርስዎ ለምን ዘርዝረው አላስረዱም ?

ጠያቂ መስፍን መኩሪያ
አዲስ አበባ

● አቶ መስፍን መኩሪያ ስለላኩልን ጥያቄና አስተያየት እናመሰግናለን “ጥምቀት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ” በሚል ርእስ እንዲጻፍ ያስፈለገበት ምክንያት ፩ኛ/ በዓለ ጥምቀት በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ፣ በአንግሊካንና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደሚከበር ፪ኛ/ እነዚሁ አብያተ ክርስቲያናት ለተከታዮቻቸው ሥርዓተ ጥምቀትን መቼና እንዴት እንደሚፈጽሙ ለማሳወቅ ነው የየአብያተ ክርስቲያናቱ ካህናትም ለአቀረብንላቸው ጥያቄ የተብራራ መልስ በመስጠት የየቤተ ክርስቲያናቸውን በዓል አከባበርና የሥርዓተ ጥምቀት አፈጻጸም አስረድተዋል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ከሌላው ጋር ለማዛመድና ለማቀራረብ የተሞከረበት አንቀጽ የለም ለእርስዎም የመሰለዎት የትኛው አንቀጽ እንደሆነ አልገለጡም የመጽሔቱ አላማ ግን ልዩነቱን ለማሳወቅ እንጂ ለሌላ አይደለም ። ልዩነቱም በሚገባ ተገልጦአል ጽሑፉን ደጋግመው ይመልከቱ ፤

፪ኛ/ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት እንዲሁም በክርስቶስ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን አንዲት ጥምቀትም አንዲት እንደሆነች ያምናሉ ልዩነት የመጣ በአራተኛው ምእት ዓመት ከኬልቄዶን ጉባኤ ወዲህ ነው “ለምን ተለያዩ” ለሚለው ግን ይህን ዘርዝሮ ለማስረዳት በዚህ ዓምድ ስለማይቻል የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ይመልከቱ ።

፫ኛ/ በጽሑፉ ማጠቃለያ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮችዋን በ፵ እና በ፹ ቀን የምታጠምቅበትን ምክንያት ለምን ዘርዝረው አላስረዱም ? ለተባለው አሁንም ለመግለጽ የተፈለገው በአጭሩ ወንድ በ፵ ሴት በ፹ ቀን ፣ ይሞታል ተብሎ የሚፈራ ሲያጋጥም ግን ከዚያ በፊት በማንኛውም ቀን በሞግዚት ወደቤተ ክርስቲያን ተወስዶ እንዲጠመቅ ሥርዓትዋ መሆኑን ነው ። ዝርዝር ምክንያቱ ግን ሰፊ ጥናትና ትምህርት ስላለው ራሱን ችሎ በሌላ ጊዜ እንዲወጣ ስለታሰበ ነው ።

**ለትንሣኤ መጽሔት**
**አዲስ አበባ**

በሲዳሞ ክ/ሀገር በቦረና አውራጃ በነገሌ ከተማ በሚገኘው ባሕረ ጥምቀት ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሰረት በዚህ ርእሰ ከተማ ከምትገኘው የነገሌ ኪዳነ ምህረት ቤተመቅደስ የሚገኙ ታቦታት ወጥተው በባሕረ ጥምቀቱ ሳሉ የከተማና የአካባቢው ሕዝብ የአራተኛው ክፍለ ጦር አባሎች በዓሉን ለማክበር በቦታው ተገኝተው ነበር ።

ለበዓሉም ከተሰበሰቡት ምእመናን መካከል እመት ብዙነሽ ወልደየስ የተባሉት ሴት የዋጋው ግምት ብር ፮፻ (ስድስት መቶ ብር) የሆነ የእጅ ካቴና ወርቅ ከእጃቸው አስረው ኖሮ ይኸው ወርቅ ላልቶ ከእጃቸው ወልቆ ሲወድቅ ሣያውቁት ዝም ብለው ወደፊታቸው ይሄዳሉ ። በዚህ ጊዜ ከኋላቸው የነበረው ወ/ር አሻግሬ ዱባለ የተባለው ምእመን አይቶት ኖሮ ሴትዮዋን ጠርቶ ንብረታቸውን አንስተው እንዲወስዱ ይነግራቸዋል ሴትዮዋም ደንግጠው ከተመለሱ በኋላ ካቴና ወርቃቸውን እንዳለ አንስተው በእጃቸው አግብተው ይሄዳሉ።

ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ወታደር አሻግሬ ዱባለ የወርቅ ነፀብራቅና ክቡርነት የዋጋውም ብዛት ሳያሣሣው ባለንብረቷን ጠርቶ እንዲያነሱ በማድረጉ የሚመሰገን ነው ።

በተቃራኒው ደግሞ አንዳንድ ፍቅረ ንዋይ ያታለላቸው እንኳንስ ወርቅን ያህል ክቡር እቃ ከሚዳ ወድቆ አግኝተውና እንዲያውም አጥር ሰብረው ቤ ቤት ሰርስረው ሰውን አታለው ያልደከሙበትን ንብረት ሲዘርፉ ይታያሉ ። ይህ ወታደር ግን ለጊዜው ሊደሰትበት ይችል እንደነበር የታወቀ ነው ። ነገር ግን በሰው ንብረት ልደሰት የማለት ፍላጐትን እምዘግዝጐ በመጣልና በሌላው ገንዘብ ልጠቀም ልደሰት የሚለውን ሰይጣናዊ ልቡና “አትስረቅ የባልንጀራ

ተከታዩን በ፲፮ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ወርኃ ክረምት

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዜማ ሊቃውንት ባሕል የኢትዮጵያ ክረምት ከሰኔ ፳፮ ቀን እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ነው ። እነዚህ ሦስት የክረምት ወራት በሰባት ንዑስ ክፍል ዘመን ይከፈላሉ ።

ይኸውም ፩ኛ/ ከሰኔ ፳፭ እስከ ሐምሌ ቂርቆስ(ሐምሌ ፲፱ ቀን) ያሉት ሳምንቶችናቸው ፤ በነዚህ ሳምንቶች ዘርአን ፤ ደመናንና ዝናምን የሚያዘክሩ ምንባባት ይነበባሉ መዝሙራትም ይዘመራሉ ፤ ምክንያቱም ዘርእ የሚዘራበት ዝናማትና ደመናት ምድርን የሚያለመልሙበት የመጀመሪያው ክፍለ ክረምት ስለሆነ ነው ።

በዚህ ክፍለ ክረምት የሚዘመሩ መዝሙራት "ደምፀ እገሪሁ ለዝናም ሰበ ይዘንም ዝናም ይትፌሣሑ ነዳያን ፤ ይጸግቡ ርኁባን የዝናም ድምፁ ተሰማ ዝናም በዘነመ ጊዜ ችግረኞች ይደሰታሉ ረኃብተኞች ይጠግባሉ ፤" (ድጓ) "ሰማዩን በደመናት ይሸፍናል ለምድርም ዝናምን ያዘጋጃል ። ሣርን በተራሮች ላይ ያበቅላል ፤ ለምለሙንም ለሰው ልጆች ጥቅም ። ትልምዋን ታረካለህ ፤ ቦይዋንም ታስተካክላለህ በነጠብጣብህ ታለሰልሳታለህ ፤ ቡቃያዋንም ትባርካለህ ።" መዝ ፴፯ ቁ.፰ ፤ ፷፬ ቁ፲ የሚሉና የመሳሰሉት ሲሆን የሚነበቡ ምንባባትም ".... ሰማዩም ዝናምን ሰጠ ምድራቱም ፍሬዋን አበቀለች" ያዕ.፭፡፲፰"... ዘሪ ዘሩን ሊዘራ ወጣ ... " ሉቃ ፰፡፭"...ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናም የምትጠጣ መሬት ፤ ለሚያርሱአትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለች ፤ እሾህንና ኩርንችትን ግን ብታወጣ የተጣለች ናት ። ለመርገምም ትቀርባለች መጨረሻዋም መቃጠል ነው ።" ዕብ. ፮፡፯-፰ የሚለውና የመሳሰለው ሁሉ ነው ።

፪ኛ/ ከቂርቆስ እስከ ማኅበር (ከሐምሌ ፲፱-ነሐሴ ፲ ቀን) ያለው ክፍለ ክረምት ነው በዚህ ክፍለ ክረምት የመብረቅን የነጐድጓድን ፤ የባሕርን የአፍላግንና የጠልን ጠባይዓት የሚያመለክቱ መዝሙራት ይዘመራሉ ምንባባትም ይነበባሉ ። በዚህ መሠረት "ምድርኒ ርእዮቶ ወአእኰተቶ ባህርኒ ሰገደት ሎቱ ምድር አየችው አመሰገነችውም ። ባሕርም ሰገደችለት"(ድጓ) "በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ሁሉ እግዚአብሔር የወደደውን ያደርጋል ። ምድርን ጐበኘሃት አጠጣሃትም ብልጽግናዋንም እጅግ አበዛህ የእግዚአብሔር ወንዝ ውሃን የተመላ ነው ። ከምድር ዳር ደመናትን ያወጣል በዝናም ጊዜ መብረቅን አደረገ ነፋሳቱንም ከመዛግብቱ ያወጣል ።" መዝ.፷፬፡፱ ፩፻፴፬፡፮-፯ በማለት እግዚአብሔር በነጐድጓድና በመብረቅ በባሕርና በሐይቅ ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው አምላክ መሆኑንና የሚታዩና የማይታዩ ፍጥረታት ሁሉ የኃይሉ መግለጫዎች እንደሆኑ የሚያስተምሩ መዝሙራት ይዘመራሉ ።

፫ኛ/ ከማኅበር እስከ አብርሃም (ከነሐሴ ፲-፳፮ ቀን) ዕጉለ ቋዓት ደስያት ዓይነ ኩሉ ይባላል ይህ ክፍለ ክረምቱ እየተገባደደ ውሃው እየጠራ መሬቱ እየረጋ ደመናውና ጉሙ እየተቃለለ የወንዞች ሙላት እየቀነሰ በውሃ ሙላት ተውጠው የነበሩ ደሴቶች የሚታዩበትና የክረምት ምግባቸውን ይዘው በየዋሻው የከረሙ ጭልፊቶችና የአሞራ ልጆች ድምፃቸውን እያሰሙ ምግብ ፍለጋ ሲወጡ የሚታዩበት ወቅት ነው ። ስለዚህም "የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ አንተ እጅህን ትዘረጋለህ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ ። ለሚጠሩት ለቁራዎች ጫጩቶች ለእንስሳትም ምግባቸውን ይሰጣል ።" በማለት እግዚአብሔር ትንሹንም ትልቁንም ማንኛውንም ፍጥረት የሚመግብ ደግ አምላክ መሆኑንና ፍጥረታትም ሁሉ እርሱን ተስፋ የሚያደርጉ መሆናቸውን የሚገልጡ መዝሙራት ይዘመራሉ ምንባባትም ይነበባሉ ።

፬ኛ/ ከአብርሃም እስከ ዮሐንስ(ከነሐሴ ፳፱ -ጳጉሜ ፭ ቀን ጎሕ ነግህ ፤ ጽባሕ ፤ ብርሃንና መዓልት ይባላል የክረምቱ ጭፍና አልፎ የፀሐይ ብርሃን ወለል ብሎ ይወጣል ጉምና ደመና በየቦታቸው ይሰበሰቡና ጥቁር ሰማይ በከዋክብት አሸብርቆ ይታያል ። በክረምቱ የውሃ ሙላት ምክንያት ግንኙነት አቋርጠው የነበሩ ወገኖች ሁሉ በዚህ ክፍለ ጊዜ ብርሃን ስለሚያዩ መገናኛ መንገዶችንም ስለሚያገኙ ክረምቱ እንደ ሌሊት ይህ ክፍለ ክረምት እንደ ንጋት ይታያል ከዚህም የተነሣ "ጎሕ ነግህ ጽባሕ ብርሃን መዓልት" ይባላል ።

፭ኛ/ ከመስከረም ፩-፰ ዮሐንስ ይባላል ምክንያቱም የዮሐንስ ስብከት ከብሉይ ወደ ሐዲስ መሸጋገሪያ ድልድይ ነው ። ስለዚህም አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱ ዓመት በሚተካበት ወቅት የዮሐንስ ስብከት ይሰበካል ትምህርቱም ይነገራል ።

፮ኛ/ ከመስከረም ፱-፲፮ "ፍሬ" ይባላል በዚህም ወቅት ምድር ስለምታበረክተው ፍሬ እግዚአብሔርም ፍሬዋን እንዲባርክና እንዲያበዛ ይጸለያል ይዘመራል ። ጸሎቱና መዝሙሩም "አቤቱ የምድርን ፍሬዋን ባርክ ምድር ፍሬዋን ሰጠች አምላካችን እግዚአብሔርም ይባርከናል ። እግዚአብሔር በጎ ነገርን ይሰጣል ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች ።" መዝ.፷፮፡፮፡፹፬፡፲፪ የሚልና የመሳሰለው ነው ።

፯ኛ/ ከመስከረም ፲፯-፳፭ ቀን መስቀል ይባላል በዚህም ወቅት መስቀል ለክርስቲያኖች ኃይልና ጽንዕ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ሰማይ ዝናም ለዘር ጠልለመከር እንዲሰጥ ምድርም የዘሩባትን እንድታበቅል ፤ ወንዞች ከመጠን አልፈው እንዳይሞሉና ጐርፍ አዝርእትንና ዕፅዋትን ሰዎችን እንስሳትን እንዳያጠፉ እዘውትራ ትጸልያለች ። ጸሎትዋም " ... በሚፈለግበት ቦታ እግዚአብሔር ዝናሙን ያዘንም ዘንድ ስለ ዝናም እንማልዳለን ። የወንዙን ውሃ ምላልን ብለን እግዚአብሔር እነሱን እስከ ልካቸውና እስከ ወሰናቸው ይመላ ዘንድ ስለ ወንዝ ውሃ እንማልዳለን ። ለዘርና ለመከር ሲሆን እግዚአብሔር ለምድር ፍሬዋን ይሰጣት ዘንድ ስለ ምድር ፍሬ እንማልዳለን ።" የሚል ነው ተገቢ ጸሎት ነው ሰዎች ሁሉ ሊጸልዩት ሊማሩትና ሊያስተምሩት የሚገባ የወርኃ ክረምት ጸሎትና ትምህርት ነው ።

# የቤተ ክርስቲያን ሕይወት

የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የሕይወት እስትንፋስና የአኗኗርዋ መታወቂያ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ነው የቅዱስ ያሬድ ዜማ ለአንድ ቀን እንኳ ቢለያት ግን የቤተክርስቲያናችን ሕይወታዊ እንቅስቃሴ ጭጭ እርጭ ብሎ እንደበትዋ እንደተያዘ ያሕል ይቆጠራል ።

ቅዱስ ያሬድ በፀዋትወ ዜማ ድርሰቱ ለቤተክርስቲያናችን ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ባለውለታ ነው ። ነገር ግን ለዚህ ታላቅ ደራሲና የፀዋትወ ዜማ አባት ለሆነው ቅዱስ ያሬድ ምንም እንኳን ታቦት የተቀረጸለት ቤተክርስቲያን የታነጸለት ቢሆን ጽላቱ ያለበት መታሰቢያው የሚከበርበት ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን ድረስ በዘመናዊ መልክ በሚገባ ባለመታነጹ በታሪክ ፊት ተወቃሾች ከመሆን አድርሶናል ። ቅዱስ ያሬድ ከሠለጠኑት አገሮችየ አንደኛው ዜጋ ቢሆን ኖሮ ምንዓይነት መታሰቢያ እንደሚቆምለትና ዝናው ከሌሎቹ ታላላቅ ደራስያን በላይ ተጋኖ እንደሚነገር አንጠራጠርም ።

ለምሳሌ በዓለም ከታወቁት ደራስያን ጋር ቢነፃፀር የቅዱስ ያሬድ የቅኔ የመጻሕፍት ትርጉምና ዜናድርሰቱ ከሁሉ የበለጠ ከመሆኑም የተነሣ መታሰቢያው ከሁሉ የላቀ ልዕልና ያገኝ ነበር ።

የዓለምን ታሪክ ስንመለከት ብዙውን ጊዜ ለታላላቅ ደራስያን ለሙዚቀኞችና ለሥነ ጽሑፍ ሰዎች ብቃት ያለው ወሮታ መመለስ ባይቻልም በመጠኑ መታሰቢያ እንዲኖራቸውና ታሪካቸው በዓለም ገንኖ እንዲታወቅ በማድረግ ረገድ ከመላው ዓለም ሕብረተሰብ መካከል ጥቂቶቹ ሴቶች የሠሩት በጐ ሥራ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

ለምሳሌ ከ፲፭፻፷፬-፲፮፻፲፮ ዓ.ም. የነበረው ታላቁ የእንግሊዝ የትያትርና የቅኔ ደራሲ ዊሊያም ሸክስፒር ፴፯ የትያትር ፭ የቅኔ መጻሕፍት በመድረስ ታሪክ ሠሪ ሆኖ ካለፈ በኋላ አስታዋሽ አጥቶ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ተረስቶ ቆይቶ ነበር ። ነገር ግን የእንግሊዝ አገር ሴቶች ከ፩፻ ዓመት በኋላ በበጐ ፈቃድ ተነሳስተው መታሰቢያ ሐውልት ስላቆሙለት ታሪኩ በአንድ ጊዜ ተጋንኖ በመነገሩ በመላው ዓለም ተወዳዳሪ የማይገኝለት የታላቅ ደራሲነትን ዜና ለማስገኘት ችሏል ።

እንዲሁም ሞዛርት የተሰኘው የኦስትራሊያ ሙዚቃ ደራሲና ዜማ አዋቂ ድምፃዊ በተነሳበት ዘመን የነበረችው ሚሪያቴሪሳ የተባለችው ንግሥት እንዳንት ላለው ድምፃዊ የዜማደራሲ ልጇን ብድርለት እንኳን አይቆጨኝም ባለችው ጊዜ እኔ ትንሽ የድኃ ልጅ ስሆን እንዴት ይህን ትመኛለሽ ቢላት " አንተም እኮ የሙዚቃ ንጉሥ ነህ" ስትል መለሰችለት ይባላል ።

ይህም የሚያመለክተን ሴቶች ለዜማ ደራስያን የሚሰጡት ክብር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ለመገመት የሚያስችል ነው ።

ታዲያ እኛስ የኢትዮጵያ ሴቶች በታላቁ የዜማ ደራሲ የቅኔ ትምህርት አባት ለሆነው ቅዱስ ያሬድ የምናቆምለት መታሰቢያ የታሪኩ መታወቂያ ምንድን ነው? በጐ ፈቃድ ካለን ልናደርገው የሚገባ ቁም ነገር አለ ይኸውም በነቢዩ ኢሳያስ ትንቢት ፶፯-፬-፯ እንደተጻፈ ለልዩ ልዩ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ መታሰቢያ የሚሆን ቤተ እግዚአብሔር በስማቸው እንዲታነጽ ተፈቅዶአል። እንግዲያውስ ለዚህ የፀዋትወ ዜማ አባት ለሆነው ለቅዱስ ያሬድ ቤተክርስቲያን ሕንፃ ሥራ ፍጹም ትብብር እንዲኖረን ያስፈልጋል ቤተ ክርስቲያናችን ያለርሱ የሚኖራት ታዋቂነት ዝቅተኛ ሆኖ ነው የሚገኘውና ።

ደግሞ ይህን በምናደርግበት ጊዜ ለቅዱስ ያሬድ መታሰቢያ የሚሆን ቤተ ክርስቲያን መሥራታችን ብቻ ሳይሆን በርሱ ዜማ የተቃኙ ድርሰቶችን ለማጥናት ድጓ፣ጾመ ድጓ፣ዝማሬ መዋሥዕትን አቋቁም የቅዳሴዜማ ለመማር እስከቤተልሄም ዙራአምባ ደብረዓባይናስለልኩላ ድርስ በመጓዝ የልመና እንጀራ ለማግኘት ከውሻ ጋር ሲታገሉ የሚኖሩትን ብዙዎችን የሕዝብ ልጆች ከድካም ለማዳን በዚሁ ባቅራቢያ ት/ቤት እ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፭ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ያዕቆብ የጌታችን ወንድም ለምን ተባለ?




የጌታችን ወንድሞች እየተባሉ የሚ ጠሩ አራት ሰዎች እንደአሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ፡፡ እነርሱም ያዕቆብ ፤ ይሁዳ ፤ ዮሳና ሳምዖን ናቸው /ማር ፮ ፤ ፫ ፡፡ ከእነርሱም መካከል ያዕቆብ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ቦታ "የጌታ ወንድም" በመባል ተጠቅሶአል ፡፡ በዚህም እትም ለመጻፍ የተፈለገው ስለ ያዕቆብ ነው ፡፡ ያዕቆብ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም መባሉ በምንና እንዴት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አያስረዳም ፡፡ ታዲያ ለምን የጌታ ወንድም " ተባለ?

ያዕቆብ በሁለት ዓይነት መንገድ የጌታ ወንድም እንደሚባል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ፡፡ ይኸውም አንደኛ በተዘምዶ ሲሆን ሁለተኛ አብሮ በማደግ ነው ፡፡ ተዘምዶውም እንደሚከተለው ነው ፡፡ ከላይ የዝምድናው ራስ አልአዛር ነው ፡፡ አልአዛር ቅስራንና ማትያን ይወልዳል ፡፡

ቅስራ ኢያቄምን ኢያቄም እመቤታችንን እመቤታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልዳለች ፡፡

ማትያን ደግሞ ያዕቆብን ያዕቆብ ዮሴፍን ዮሴፍም የጌታ ወንድም" እየተባለ የሚጠራውን ያዕቆብን ይወልዳል ፡፡ ይህም በሥዕላዊ መግለጫ ሲታይ እንደሚከተለው ነው ፡፡




ዝምድናው በዚህ ዓይነት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችንና እመቤታችን በያዕቆብ አባት በዮሴፍ ቤት ይኖሩ ስለነበር ጌታችንና ያዕቆብ አብረው አድገዋል ፡፡ በዚህም ምክንያት የጌታ ወንድም መባሉን ትውፊት ያስረዳል ፡፡

ያዕቆብም የጌታ ወንድም ተብሎ መጠራቱ በሌሎች እንደበት እንጂ በጌታችን ወይም በእመቤታችን አንደበት አይደለም ፡፡ ራሱ ያዕቆብ እንኳ መልእክቱን ሲጽፍ" ... የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ " ከማለት በቀር ራሱን የጌታ ወንድም ብሎ አልጠራም ፡፡ ምክንያቱም እመቤታችን ዘላለማዊት ድንግል ስትሆን ጌታችንም በቀዳማዊ ልደቱ ተቀዳሚና ተከታይ እንደሌለው ሁሉ በደኃራዊ ልደቱም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው ዋሕድ ወልድ ነውና ፡፡ ነገር ግን ያዕቆብ የጌታ ወንድም መባሉ ከእመቤታችን ስለተወለደ ነው በማለት የሚያወሩ አንዳንድ መስተቃውማን የእግዚአብሔርን ቃል እንደራሳቸው ሀሳብ ያጣምማሉ ፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ወልድን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደምትወልድ ከዚያም በኋላ ለዘለዓለም በድንግልና ጸንታ እንደምትኖር በመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን የትንቢት ቃል ይለውጣሉ ፡፡ ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የጸኑ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ለማመን ያስቸግራል ፡፡

ያዕቆብ እንደሌሎቹ ሐዋርያት በመጀመሪያ የተጠራ ሐዋርያ አይደለም ፡፡ ሆኖም ከሐዋርያት ጋር አብሮ ጌታን ይከተል ስለነበረ እነርሱ ያዩትን ሁሉ አይቶአል/ ዮሐ ፪ ፡ ፲፪ ፡ ማር. ፫.፴፩-፴፫/

ግን እስከ ትንሣኤ ድረስ አማኒ እንዳልነበረ በዮሐ.7.፩-፭ ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት ሊቃውንት ያትታሉ ፡፡

ያዕቆብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተያዘባት ሌሊት ጀምሮ ከሞት ተነስቶ እስካየው ድረስ እህልና ውሃ ለአለመቅመስ ወስኖ ነበር ጌታችንም ከሦስት ቀን በኋላ ከሞት ተነስቶ " የሚበላ አለህን ሲል ያዕቆብን ጠየቀው ያዕቆብም በታላቅ ደስታ ተሞልቶ እንጀራ አቀረበ ፡፡ ጌታችንም የቀረበውን እንጀራ ባርኮ ለያዕቆብ ሰጠው ፡፡ በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ተጽናና በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስም አመነ ፡፡ ከሐዋርያትም እንደ አንዱ ሆኖ ለትንሣኤው ምስክር ሆነ /፩ቆሮ ፲፭ ፡ ፯/

ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ለመጀመሪያ ጊዜ ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ እንዲሆን በሐዋርያት ተመርጦ እስከ ፍጻሜ ሕይወቱ ሲመራ ኖሯል ፡፡

ቅዱስ ጴጥሮስ ከእስር ቤት በወጣ ጊዜ በእግዚአብሔር ኃይል መፈታቱን ያስታወቀ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ለነበረው ለያዕቆብ ነበር ፡፡ ምክንያቱም ጳጳሱ ያዕቆብ እስረኛው ጴጥሮስ እንዲፈታ ሌሊትና ቀን በትጋት ይጸልይ ነበርና ስለዚህ ቅዱስ ጴጥሮስ በያዕቆብ ጸሎት በእግዚአብሔር ምሕረት መፈታቱን በቅድሚያ ለጳጳሱ ለያዕቆብ አስታወቀ ፡፡ የሐዋ. ፲፪ ፡ ፲፯ ፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ በኢየሩሳሌም ላይ በተደረገው የሐዋርያት ሲኖዶስ ጉባዔ ላይ ያዕቆብ መሪ ከመሆኑም በላይ ወደ ክርስትና እምነት ለተመለሱ አሕዛብ ሥርዐት እንዳይከብዳቸው ሀሳብ ያቀረበ ሐዋርያ እርሱ ነበር ፡፡

ያቀረበው ሀሳብ እንዲህ የሚል ነበር ፡፡ "ከሐአዛብ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን እንዳናስቸግራቸው ...... እንድንጽፍላቸው እቆርጣለሁ" የሐዋ 15፡19/ ፡፡ ሀሳቡ የመንፈስ ቅዱስ ነበርና ጉባኤው በሙሉ ተስማምቶ አጽድቆታል ፡፡

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ካመነ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢየሩሳሌምን ሲጎበኝ ያዕቆብን ተገናኝቶአል ፡፡ ያዕቆብም አዲሱን አማኒ ጳውሎስን አጽናንቶታል ፡፡ /ገላ. ፩. ፲፱/ እንደገናም ከ፲፬ ዓመት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ የጌታ ወንድም የተባለውን ያዕቆብን ከዮሐንስና ከጴጥሮስ ጋር አግኝቶ ማነጋገሩን በገላ ፪ ፱ ላይ ገልጦአል ፡፡ በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ ያዕቆብ ዐምደ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን መስክሮአል ፡፡

አዎ አይሁድ ይገፋአት የነበረችውን የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን አጽናንቶ ደግፎ የያዛት ያዕቆብ ነበር ፡፡ ስለዚህ ጽኑ ዐምድ ተብሎአል ፡፡

ሐዲስ ኪዳን ስለ ያዕቆብ የሚናገረው ይህ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ደግሞ የሚከተለው ተገልጦአል ፡፡ ሄጌስጽዮስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ እንደ ጻፈለት ያዕቆብ በሕይወቱ ሁሉ ወይንና ሌላ ጠንካራ መጠጥ አልጠጣም ሥጋ አልበላም ፡፡ ምላጭም በራሱ ላይ አልወጣም ፡፡ ዘይትም ፈጽሞ ተቀብቶ አያውቅም ነበር ፡፡ እንደ ዚህም የሆነው ጌታችን በዕለተ ትንሣኤ ከተገለጠለትና ካመነ ሐዋርያም ከሆነ በኋላ ነው ያዕቆብ ዘወትር ቆሞ ከመጸለይና ከመስገድ የተነሣ ጉልበቱ እንደ ግመል እግር ሆኖ ነበር ስለርኅራሄውና ሕዝቡን በፍቅርና በትህትና ስለመጠበቁ እውነተኛው የሕዝብ ጠበቃ እየተባለ ይጠራ እንደነበር ሄጌስጽዮስ ጽፎአል ኤሴብዮስ የቤ/ክ/ታሪክ ፪.፳፫/

ያዕቆብ በዚህ ዓይነት የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን ሲመራ በ፷፪ ዓ.ም. ፊስጦስ የተባለው ሮማዊው የገሊላ ገዥ ሞቶ አልቢኖስ እስኪመጣ ድረስ አናንዮስ የተባለው ሊቀ ካህናት አጋጣሚ ጊዜ አገኘ ፡፡ ያዕቆብንም አስጠርቶ "አሪትን ተቃውሞአል በአራት ቦታ ወንጌልን አስተምሮአል ክርስቶስ ተነሣ ብለህ መስክረሃል" በማለት በአደባባይ በድንጋይና በዱላ ተደብድቦ እንዲሞት ለሕዝበ አይሁድ አሳልፎ ሰጠው ፡፡

አይሁድም በሊቀ ካህናቱ በአናንዮስ ትእዛዝ መሠረት በድንጋይ ወገሩት በዚሁ ምክንያት ቅዱስ ያዕቆብ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፷፪(፶፭) ዓ.ም. በሰማዕትነት ዐርፎአል ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ሐምሌ ፲፰ ቀን ቅዱስ ያዕቆብ ን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ፡፡ ጻድቅና ቅዱስ ሐዋርያ እንደመሆኑ መጠን አማላጅነቱ ን አምና ትቀበላለች ፡፡

"እምነት ያለ ምግባር ምግባርም ያለ እምነት ከንቱ ነው ነፍስ እንደተለየችው ሥጋ ነው" በማለት ቅዱስ ያዕቆብ በአስተማረው ትምህርት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጸንታና ተጠብቃ ትኖራለች ፡፡ ሌሎችም በቅዱስ ያዕቆብ ትምህርት መሠረት እምነትና ምግባር ን አስተባብረው እንዲይዙ ታስተምራለች ፡፡ ለመጀመሪያ ዋ ቤተ ክርስቲያን ዐምድ የነበረው ያዕቆብ ዛሬም ለአለችው ለእውነተኛዋ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዐምድ ነውና

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

## የቤተ ክርስቲያን ሕይወት

ከገጽ ፫ የዞረ

ንዲሠራላቸው ማድረግ ይቻላል ፡፡ ይህም ከሆነ "ተማሪ በሞተ በሰባት ዓመቱ ተምሮ ይመጣል ትላለች እናቱ" እየተባለ የሚነገረውን ሙሾ ከመስማት ያድናል የቅዱስ ያሬድን ዜማ ለመማር ከአገር አገር በመዞር ሕይወታቸውን የሚያጠፉ ወገኖቻችንን ከሞት ማትረፍ የሚቻለው የርሱ መታሰቢያ የሚሆን ት/ቤትና ቤተክርስቲያን በየአካባቢው በማቋቋም ስለሆነ እጃችንን በመዘርጋት ለዚህ በጐ ሥራ ሁላችን እንድንተባበር በቅዱስ ያሬድ ስም እንጠይቃለን ፡፡

"እግዚአብሔር አምላክ ለቅዱስ ያሬድ የሰጠው በረከትና ፀጋ ለሁላችሁ ይብዛላችሁ አሜን ፡፡

ሲስተር ፋንታዬ አሻግሬ

## ብርሃን ዓለም ጳውሎስ

ከገጽ ፰ የዞረ

ይህ ነው የመልእክቱ ማስረጃ ሁሉ ይህ ነው ፡፡ እንዲህ እጽፋለሁ ፪ኛ ተሰሎ.፫. ፲፯ ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በሰላምታ አቀራረቡ የሚጽፈውን ሁሉ ቦታውን አድራሻውንና ጊዜውን እየለየ በመጻፉ በአሁኑ ጊዜ በሰለጠነው ዓለም እንኳ እንደቅዱስ ጳውሎስ ጥንቃቄ የተመላው አጻጻፍ ሊኖር እንደማይችል የሚያስገምተው በመሆኑ ከምሁርነቱ ጋር ሥራውን ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያከናውንለት መሆኑን እንረዳለን ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ አስራ አራት መልእክታትን የጻፈ ሲሆን እነዚህን መልእክታት ቅዱስ ጳውሎስ ለሌሎች እየነገረ አስጽፎአቸዋል የሚልየአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት አስተያየት አለ ፡፡ በመጨረሻ የሚገኙትን ሰላምታዎች ግን የሚጨምራቸው ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ለመሆኑ ከላይ የጠቀስናቸው ጥቅሶች ያስረዳሉ ፡፡

"ይህንን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ ሲል ይገኛልና ፡፡ ሮሜ.፲፮.፳፪ የገላትያ መልእክት ግን በቅዱስ ጳውሎስ የተጻፈ ለመሆኑ "እንዴት ባሉ ታላላቅ ፊደላት በእጄ እንደጻፍሁላችሁ እዩ ገላ ፮፡፲፩ ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሁሉ ታላቅ ሐዋርያዊ ተግባር ከፈጸመ በኋላ ሐምሌ ፭ ቀን ፷ ዓ.ም በሰማዕትነት አርፎአል ፡፡

ተስፋ ጥሩነህ





www.ethiopianorthodox.org

# « አይ፟ዟችሁ አትፍሩ »

ፍርሃት ከየት መጣ ? እንዴትስ ከሰው ልጅ ጋር ሊዛመድና በሰው ልብ ሊቀረጽ ቻለ? ብለን ብንጠይቅና ቅዱሳት መጻሕፍትን ብንመረምር ፍርሃት የመጣው በሐሳብ ተጸንሶ በተግባር በተገለጸው በኃጢአት ምክንያት መሆኑን እንገነዘባለን "እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ? አለው እሱም በገነት ድምፅህን ስለ ሰማሁ ዕራቁቴንም ስለ ሆንኩ ፈራሁ ተሸሸግሁም ይላል ዘፍጥ.፫፣፱-፲ ።

እነሆ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የፍርሃት መንፈስ በሰው ላይ ይናራል እንግዲህ ፍርሃት በዲያብሎስ ዘሪነት የበቀለና ከጊዜ በኋላ የመጣ የኃጢአት ፍሬ ነው ለማለት ይቻላል ። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ሲፈጥረው የእግዚአብሔርን መልክ አስይዞ የፍርሃት መንፈስ ያልተቀላቀለበት ሕያው ፍጥረት አድርጎ ፈጠረው እንጂ ፍርሃትና ድንጋጤ የተቀላቀለበት አልነበረም ከተፈጠረ ከጥቂት ዘመናት በኋላ ግን የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍና ትእዛዙን በማፍረስ ኃጢአት ሠራ በዚህ ጊዜ ታላቅ ኃጢአትን በመሥራቱና እግዚአብሔርንም በማሳዘኑ ፍርሃት አደረበት ከዚያች ሰዓት ወዲህ ድምፅ በሰማ ቁጥር የሰው ልጅ ሲፈራ ሲደነግጥ ይኖራል ።

በተለይ በጨለማና የሰው ድምፅ በማይሰማበት ሲሄድ ከባድ ፍርሃት ይሰማዋል ታዲያ የዚህ ዓይነት ፍርሃት በሰው ሊዘመት የቻለው በሌላ ነገር ሳይሆን ከእምነት ጉድለትየተነሣ ሁኖ እናገኘዋለን ።

አንድ ጊዜ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተራራ ትምህርቱን (አንቀጸ ብፁዓንን) ፈጽሞ ከቅፍርና ሆም ተነሥቶ ወደ ጌርጌሴኖን በታንኳ ለመሻገር ወደ ታንኳይቱ ገባ ደቀ መዛሙርቱም ከእሱ ጋር በታንኳ ተሳፍረው ጉዞአቸውን እንደ ቀጠሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ ኃይለኛ ነፋስ ተነሳ በባሕሩም ታላቅ መናወጥ ሆነ በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ እጅግ ፈሩ ተስፋ እስከመቁረጥ ደረሱ ጌታ ሆይ አድነን ጠፋንኮ ማዕበሉ ሊያስጥመን ነው በማለት ሁሉም ባንድነት ጮሁ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የፍራታቸውን ብዛትና የሃይማኖታቸውን ልልነት አውቆ "እናንተ እምነት የጎደላችሁ ስለምን ትፈራላችሁ ሲል ገሠጻቸው ማቴ.8 ፣ 26 ። ከዚህ በኋላ ነፋሱንም ማዕበሉንም ሁሉን ገሠፃቸውና ጸጥ አሉ ከዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን የሰው ልጅ እምነቱ ሲላላ ምን ያህል አደጋ እንደሚደርስበትና ከታላቅ ችግር እንደሚወድቅ ነው ።

ደቀ መዛሙርቱ በከባድ ፍርሃት ተውጠው ሲጨነቁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመካከላቸው ነበር ግን በሃይማኖት ፍጹም ስለአልነበሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላችን ሳለ ምን እንሆናለን ምንስ ይደርስብናል አላሉም እንሞታለን ባሕሩ አስጥሞን ይቀራል እንጂ እንድናለን የሚል ተስፋም አልነበራቸውም ። እንግዲህ ፍርሃት በሰው ልብ የሚፈጠረው ከእምነት ጉድለት ለመሆኑ በዚህ ለማወቅ ይቻላል ።

ሰው በፍርሃት ሲሰቃይ እንዲኖርና በድንጋጤም ዕረፍት እንዲያጣ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም ከዚህም የተነሳ ከፍርሃት ነፃ የሚሆንበትን መንገድ አዘጋጅቶለታል ይኸውም ፩ኛ/ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ፍርሃትን የሚያስወግድ ሌላ እንደ ሌለ በፍጹም ልብ ማመን ነው ፪ኛ/ ቃሉን የሚጠብቅ በማንኛውም ነገር ሊፈራ አይችልም ራሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" ብሏል ዮሐ.፲፬፣፲፭

እርግጥ በእግዚአብሔር አምነው ትእዛዙን እየጠበቁ የሚኖሩት ሁሉ ሥጋዊ ፍርሃት የለባቸውም ማለት ሳይሆን ፍርሃት አይገዛቸውም ማለት ነው ። ፍጹማን ክርስቲያኖች የሆኑ ምንም እንኳን የሚያስፈራ ነገር ቢያጋጥማቸውም ሊሸበሩ አይችሉም ምክንያቱም እግዚአብሔርን በሙሉ ልባቸው ስለሚያመልኩትና በጽኑ ሃይማኖት ለሚከተሉት ወዳጆቹ የሰጠው አስተማማኝ ተስፋ ስላለ ነው ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረውን ቃል ብንመለከት ሕይወትን የሚያድስ ተስፋ እናገኛለን ይኸውም "እኔ ካንተ ጋር ነኝና አትፍራ ፣ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ አበረታሃለሁ እረዳህማለሁ በጽድቁም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ እነሆ የሚቀጡህ ሁሉ ያፍራሉ ይዋረዱማል የሚከራከሩህም እንዳልነበሩ ይሆናሉ እኔ አምላክህ እግዚአብሔር እረዳሃለሁና አትፍራ " የሚል ነው ኢሳ. ፵፩ ፣ ፲-፲፬ ።

እግዚአብሔር ለወዳጆቹና በሕጉና በፈቃዱ ለሚሄዱ ይህንን የመሰለውን ተስፋ ይሰጣቸዋል ስለዚህ ከፍርሃትነፃ ለመሆን ከእምነት የበለጠ መሣሪያ ሌላ አይገኝም በየጊዜው ችግርህን የምትነግረው የሚያስጋህንም ሁሉ በሃይማኖት የምትወያየውና ለደረሰብህም ችግር ሁሉ መፍትሔ ሊሰጥህ የሚችለውን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ እመነው እርሱንም ተከተለው ።

እርሱን አምኖ ያፈረ ፣ እሱን ተከትሎ የወደቀ አንድም አይገኝምና ከማመን ፈቀቅ ማለት አያስፈልግም ካመኑትና እግዚአብሔርን ከተከተሉት ከሃይማኖት የጠነከረ ከእግዚአብሔርም የበለጠ መጠጊያ ዓለምን ሁሉ ቢዞሩ ሌላ ምርኩዝና መጠጊያ እንደማይገኝ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ ነቢዩ ዳዊት በየትም ቢሄዱ እግዚአብሔር የሌለበት ቦታ እንደ ሌለ ሲገልጽ "ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደ ሲዖል (ምድር) ብወርድ በዚያ አለህ እንደ ንሥርም የንጋትን ክንፍ ብወስድ በዚያ አለህ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበር በዚያ እጅህ ትመራኛለች " ሲል እግዚአብሔር በሁሉ በየብስም በባሕርም በሰማያትም ሙሉ መሆኑን አብራርቶ አስረድቷል መዝ. ፩፻፴፰፣፰ ነገር ግን ት

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ



ይህ በአሕዛብ በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ ስለስሜ ስንት መከራ እንዲቀበል አመለክተዋለሁ የሐ-ሥ.፱-፲፭ ።

ቅዱስ ጳውሎስ የተወለደው ዛሬ ቱርክ እየተባለ በሚጠራው በቂልቅያ አውራጃ በሚገኘው ጠርሴስ ከተማ ነው ። ጠርሴስ በዚያን ጊዜ በሮማ ቅኝ ግዛት ውስጥ የነበረች ከበርቴ ነጋዴዎች የሚኖሩባት የባህር ጠረፍ ውብ ከተማ ነበረች ። በዚያ የሚወለዱ ወንዶች ሁሉ በዚያ በመወለዳቸው ብቻ የሮማ ዜግነት በነፃ ይሰጣቸው ነበር ።

ስለዚህም የሮማ ዜግነት የሌላቸው ሌሎች ዜጐች የዚያን ጊዜ ክብር የነበረውን የሮማን ዜግነት ለማግኘት ብዙ ገንዘብ ያወጡ ነበር ።

ቅዱስ ጳውሎስ በዚችው ከተማ ተወልዶ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ ገና ተማሪ እንደነበረ ለመረዳት ይቻላል ።

በዚህም ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎች ደቀ መዛሙርትን ሲመርጥ እርሱን አልመረጠውም ምክንያቱም ፩ኛ/ ቅዱስ ጳውሎስ ገና ተማሪ ሆኖ ከታወቀው የሕግ መምህር ከገማልያል በመማር ላይ ስለነበር ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርቱን እንዳያቋርጥ ስለአሰበ ፪ኛ/ ገና ወጣት ስለነበረ ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርቱን ሳያቋርጥ ተከታትሎ ከጨረሰ በኋላ በወንጌል ሥራ እንደሚያሰማራው ስለሚ[illegible]ቅ ትምህርቱን እስከሚጨርስ ምርጥ ዕቃ አድርጎ ስለጠበቀው ነው ።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ በሥጋ በዚህ ዓለም በነበረበት ወቅት ገና ወጣት ና ልጅ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን ።

በሌላ በኩልም ብንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በሞቱ ድል አድርጎ ተነስቶ ካረገ በኋላ እንኳ ቅ.ጳውሎስ ገና ወጣት እንደነበረ ለመረዳት የምንችልበት መንገድ አለ ይኸውም ቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ በደንጋይ ተወግሮ በሞተ ጊዜ "ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በሚሉት በአንድ ጐበዝእግር አጠገብ አኖሩ» የሐ.ሥራ ፯፣፶፰ ተብሎ ተጽፎአልና ቅዱስ ጳውሎስ በጌታ ዘመን ገና ተማሪ እንደነበረ የተረጋገጠ ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያ ትምህርቱን የተከታተለው በተወለደበት በጠርሴስ ከተማ ነበረ ጠርሴስ የብዙ አገር ነጋዴዎች የሚከማቹባት የብዙ አህጉር ዜጐች መነሀሪያ ስለነበረች ብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ነበረች ። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስም የተለያዩ ቋንቋዎች እንደተማረ ለመረዳት አያዳግትም ።

እንዲያውም የታወቀው የሕግ መምሕር ገማልያል ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄዱ በፊት በዚችው ሀብታም ከተማ ያስተምር ስለነበረ ቅዱስ ጳውሎስም ከዚሁ መምህር ገና በልጅነቱ በጠርሴስ እንደተማረ እራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ" እኔ የኪልቅያል በምትሆን በጠርሴስ ከተማ የተወለድሁ በዚች ም ከተማ በገማልያል እግር አጠገብ ያደግሁ የአባቶችንም ሕግ ጠንቅቄ የተማርሁ ነኝ" የሐ.ሥራ.፳፪፣፫ ብሏልና ከራስበላይም ስክር ሊኖር ባለመቻሉ ገማልያል በመጀመሪያ የጠርሴስ የሕግ መምህር ነበረ ማለት ነው ።

የቅዱስ ጳውሎስ ወላጆች ዕብራውያን ሲሆኑ በዘመኑ ክብር የነበረውን የሮማን ዜግነት የተቀበሉ ነበሩ ። ጠርሴስም ያን ጊዜ የሮማ ቅኝ ግዛት ስለነበረች በጠርሴስ የሚወለድ ወንድ ልጅ ሁሉ የሮማ ዜግነት እንዲኖረው በተደረገው መሠረት ቅዱስ ጳውሎስም በጠርሴስ በመወለዱ የሮማ ዜግነት አግኝቶ ነበረና የሮማ ዜግነቱ በኋላ ለተሰማራበት የወንጌል መንግሥት ሥራው እጅግ ጠቅሞታል ። ምክንያቱም ያን ጊዜ የሮማ ዜግነት የነበረው ሰው ይከበርና ይፈራ ስለነበረ በሮማ ቅኝ ግዛት አገሮች ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን ሲያስተምር መከራ በሚያከብዱበትና የወንጌል ትምህርት እንዲቋረጥ ሲያሥሩት"የሮማን ሰው ያለሕግ እንዴት ታንገላታላችሁ"በማለት ያለሕግ የሚያደርሱበትን ስቃይ እያስታወሰ የወንጌል ትምህርቱን ያስፋፋ ነበርና ነው ። የሐ.ሥ ፳፪፣፲፭-፳፰ ም-፲፮ ፣ ፴፯

ቅዱስ ጳውሎስ የኦሪትን ሕግ ጠንቅቆ የተማረ ስለኦሪት አጥብቆ የሚተጋ በመሆኑ ኦሪት እያነሰች ወንጌል እያደገች መሄድ ስትጀምር ወንጌልን ያስተምሩየነበሩ ክርስቲያኖችን ቅዱስ ጳውሎስ አጥብቆ ማሳደድ ጀመረ ።

ከዕለታት አንድ ቀን የድጋፍ ደብዳቤ ከካህናት አለቆች አስጽፎ ይዞ ክርስቲያኖችን አሳዶ ለማስያዝ ደማስቆ ወደሚባል የሶርያ ዋና ከተማ ሲሄድ ገና በመንገድ ላይ ሳለ ጌታ ተገለጠለት ።በዚያም ከጌታ ጋራ በግልጽ ተነጋግሮ ወደ ከተማ እንዲሄድ ጌታ ስለአዘዘው ወደ ከተማ በመሄድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ሕያውና የዘላለም አዳኝ አምላክ መሆኑን አምኖና ተረድቶ ተጠመቀ። የሐ.ሥራ ፱፣፩-፲፱ ከዚያም በደማስቆ ከተማ ዙሪያ ወደሚገኝ የአረብ አገር ሄዶ ሦስት ዓመት እያስተማረ ተቀመጠ ገላ.፩፣፲፯ ፣ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሰው ሳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተመረጠ በኋላ በሰማዕትነት እስከሚሞት ድረስ ስለክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት ሰፋ አድርጎ ለብ



www.ethiopianorthodox.org

ዙ ዓመታት አስተማረ ። ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ ከሌሎች ወንጌላውያንና ሐዋርያት የበለጠ መልእክታትን የጻፈ እርሱ ሲሆን በመልእክታቱ ከሕላዌ መለኮት እስከ ማንኛውም የማህበራዊኑሮ ጉዳይ ደህና አድርጎ አብራርቶ በማስተማር ጽፎአል ። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ ጳውሎስ በማህበራዊና በመንፈሳዊ ጉዳዮች ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ብንጠቅስ ብርሃነ ዓለም ተብሎ መሰየሙ ለዚያን ጊዜው ማህበረ ሰብእና ለአሁኑዋም ቤተክርስቲያን ምን ያህል አገልግሎት እንዳላቸው አስተዋይ ህሊና ያለው ሁሉ የሚገነዘበው ነው ።

እነዚህን አንዳንዶቹን እንደሚከተለው እናቀርባቸዋለን ።

፩ኛ ስለነፍስ ገዳዮች ቅጣት

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስእንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ። ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል ።

፩ኛ ቆሮ.፫፥፲፮-፲፯ ።

፪ኛ/ ስለስፖርት ጠቃሚነት

ቅዱስ ጳውሎስ በዚያን ጊዜ ጠቃሚና በሮማውያን ዘንድ ተወዳጅ የነበረውን የሩጫ ስፖርት ለሰማያዊ ስጦታ ምሳሌ አድርጎ አቅርቦታል።"በእሽቅድምድም ቦታ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን ? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ ።

፩ኛ ቆሮ.፱፡ ፳፬

፫ኛ/ ስለዝሙት ጠንቅ

ዝሙት እንዳለባችሁ ይሰማል የዚህ ዓይነት ዝሙት በአህዛብ ዘንድ እንኳ ፈጽሞ የማይደረግ ነው ። ከእናንተ መካከል የአባቱን ሚስት ያገባ አለና ። እናንተም ይህን ከሚያደርገው ጋር በድላችኋል ። ስለዚህስ ለምን አጥብቃችሁ አላለቀሳችሁምእኔበሥጋ ከእናንተ ጋር ባልኖርም በመንፈስ አብሬአችሁ ስለአለሁ ይህንን ሥራ በሠራው ሰውላይ ፈርጀበታለሁ ፩ኛ ቆሮ ፭.፩-፲፫ ።

፬ኛ/ ባለው ስለመጠቀም

የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁ እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያተርፍ ቃል ነው ። አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለመውደድ ይሁን ያላችሁም ይብቃችሁ ። ፊልጵ ፬፡፲ ፣ ፩ኛ ጢሞ. ፮፣፯ ፣ ዕብራ.፲፫፣፭ ፣

፭ኛ/ ስለ ጋብቻ

ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር በሕግ ከእርሱ ጋር የታሰረች ናት ። ባልዋ ቢሞት ግን ስለባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች ። ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነፃነት አላት ሮሜ.፯፡፪ ፣ ፩ኛ ቆሮ.፯፡፴፱ ።

፮ኛ/ ለችግረኞች ገንዘብ ስለማዋጣት

ለቅዱሳን ስለሚሰበሰበው ገንዘብ ግን ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደሠራሁ እናንተም እንዲሁ አድርጉ ። በሳምንቱ መጀመሪያ ከሁላችሁ እያንዳንዱ እንደተቻለው ያስቀምጥ እኔ ስመጣ ይህ እንዳይሆን በመጣሁም ጊዜ የመረጣችኋቸውን በጽሑፍ እሰዳቸዋለሁ ምፅዋታችሁን ወደ ኢየሩሳሌም ያደርሱ ዘንድ ነገሩ ቢቀናኝ ከእኔ ጋራ ይሄዳሉ ፩ኛ ቆሮ. ፲፮. ፩-፬ ፣ ፪ኛ ቆሮ. ፰. .፱ ፣ ገላትያ ፪ ፣ ፲ ።

፯ኛ/ ስለአምልኮ ጣዖት ከንቱነት

እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለመብላት ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን ። አንተ እውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ስትቀመጥ አንድ ሰው ቢያይህ ደካማ ሰው ቢሆን ለጣዖት የተሠዋውን ለመብላት ህሊናው አይታነፅበትምን በአንተ እውቀትም ይህ ደካማ ይጠፋል ። እርሱም ክርስቶስ የሞተለት ወንድም ነው ።

፩ኛ ቆሮ. ፰፡ ፩-፲፫ ።

፰ኛ/ ባልና ሚስት ተሳስበው መኖር እንዳለባቸው

ስለዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ ፩ኛ ቆሮ.፯፡፩-፲፮ ።

፱ኛ/ ስለ ፍቅር ጠቃሚነት

በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሿሿ ጸናጽል ሆኜአለሁ፣ ፍቅር ይታገሣል ፣ ቸርነትንም ያደርጋል ። ፍቅር አይቀናም ፍቅር አይመካም አይታበይም ፣ የማይገባውን አያደርግም ። አይበሳጭም ። ፩ኛ ቆሮ.፲፫.፩-፲፫ ም. ፲፬. ፩-፭ ፣

፲ኛ/ ስለ ትንሣኤ ሙታን

አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ተነስቶአል ። ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና ። ፩ኛ ቆሮ. ፲፭. ፳-፶፯

፲፩/ በማንኛውም ነገር መከራከርና መለያየት እንደማይጠቅም

ወንድሞቼ ሆይ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ሰምቻለሁ ይህንም እላለሁ። እያንዳንዳችሁ እኔ የጳውሎስ ነኝ ፡ እኔስ የአጵሎስ ነኝ እኔ ግን የኬፋ ነኝ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ ። ክርስቶስ ተከፍሎአልን ? ጳውሎስስ ስለእናንተ ተሰቀለን ? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን ? ፩ኛ ቆሮ. ፩፡፲ ።

በአጠቃላይ ቅዱስ ጳውሎስ ስለማይጠቅሙ ነገሮች በሰፊው ዘርዝሮ በማስተማር ለዓለም ጠቃሚና ብርሃን ሰጭ የሆነ ትምህርቱን አስተላልፎአል ።

ቅዱስ ጳውሎስ የዚያን ጊዜ ዘመን የነበረው ሥልጣኔ ደህና ሆኖ የገባው የአስተዳደርና የመጻጻፍ ሥርዓትን ጠንቅቆ ያወቀ ስለነበረ የጻፋቸውን መልእክታት ሁሉ ምልክቱ በሁሉም ዘንድ በታወቀው በጽሑፍ ፊርማው አረጋግጦ ይልካል እንጂ የጻፈውን ሳይፈርምና ምልክት ሳያደርግ አይልክም ነበር ። እንዲሁም ከመልእክታቱ መግቢያና መጨረሻ ላይ የሰላምታ ቃል ሳይጨመር ብዙ ጊዜ አይልክም ነበር ። ይህንንም እንደሚከተለው ለምሳሌ ያህል እንመልከት "በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው ። ቆላስ.፬.፲፰ በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ·

ተከታዩን በገጽ ፳ ይመልከቱ



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## ተቀዳሚ ዝግጅት

፩/ የድርሰቱ ዓይነት (ሳብጀክት)አመራረጥ

አንድ ደራሲ የሚመርጠው የድርሰት ወይም የንግግር ዓይነት ያልተለመደና የማይታመንበት ግብታዊ ስሜት ማንፀባረቂያ ሆኖ አንባቢዎችንም ሆነ አድማጮችን የሚያታልል እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ አንዳንድ ድርሰቶች ምንም ዓይነት ተጨባጭ ፍሬ ነገር ሳይኖርባቸው ውብ የሆነ አስደሳች ወይም አስደንጋጭ ርእስ ተሰጥቶአቸው የአንባቢን ዓይን ወይም ስሜት የሚማርኩ መስለው ከታዩ በኋላ በሚነበቡበት ጊዜ ባዶ የወረቀት ክምር ሆነው የሚገኙበት ጊዜ ይኖራል። ይዘት የለሽ ቅርፅ ማለትም ይኸው ነው ።

ስለዚህም እንዲህ ዓይነቱ አሳፋሪ ድርጊት ላይ ከመድረሱ በፊት አንድ ደራሲ ምናልባት ስለጤና አጠባበቅ ስለመንፈሳዊ ሕይወት ስለትምህርት ወይም ሥነ ጥበብ ስለ ባህል ስለ ሣይንስ ወይም ፍልስፍና ስለፖለቲክስ ወዘተ ... እንደ ትያትር ወይም ድራማ ዓይነትም ሆነ ታሪካዊ ቅኔ በመጻፍ ወኔን ለመቀስቀስ ከፈለገ ስለየትኛው ክፍል ዋጋ ያለው ትምህርት ለመስጠት እንደሚችል በጥንቃቄ መገምገም ይኖርበታል ። ይህንም ተምኔት ከፍጻሜ ለማድረስ ኅብረተሰብ ሊቀበለው የሚችለውን ብሔራዊና ባህላዊ የአነጋገርና የአጻጻፍ ዘዴ በትክክል ለማጤን ከሕዝብ ጋር አብሮ የመኖርን ዘዴ በመከተል ከአረጋውያን ከሊቃውንትና የንግግር ወይም የሥነ ጽሑፍ ችሎታ ባላቸው ሁሉ በመጠየቅ ልምድ መቅሠምና በተለይም ለረጅም ጊዜ ቢያንስ ከአንድ መቶ በላይ ብዛት ባላቸው ደራስያን የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብን ይጠይቃል ።

፪/ የርእስ አመራረጥ ተግባር

የድርሰቱ ዓይነት ምንነት በትክክል ከተገመገመ በኋላ በሁለተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ዋና ነገር በድርሰቱ ውስጥ የሚቀርበውን ሐሳብ ባጠቃላይ የሚያቅፍ አንድ ወጥ የሆነ ርእስ የመምረጡ ጉዳይ ነው ። ይህም ሲሆን ዋናው ርእስ የድርሰቱ አካል መከፋፈያ ከሆኑት ከውስጥ አርእስቶች የተለየ መሆን አለበት።

በተለይም ስለግልጥነቱና ዕውነትን የሚያንፀባርቅ ስለመሆኑ ከጊዜውም ሁኔታ ጋር የሚስማማና የሚያሻማ ትርጉም የሌለው ቀጥተኛ ሐሳብ ተሸካሚ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ።

፫/ የቋንቋ ጥራትና አጠቃቀም ዘዴ

ጉንዳን እንኳ የሚመገበውን ነገር ጠቃሚውንና ጐጂውን ሳይለይ እሠሡን ገሠሡን አጋብሶ ወደጉሬው አያስገባውም ። አንድ ደራሲም በመዝገበ ቃላት የተጻፈውን ወይም ከገጠር እስከ ከተማ የሚነገረውን ተራና መናኛ አልባሌ ቃል ሁሉ እንዳገኘ አይጽፍም ። ውበትና ግልጥነት ያለውን ቃል ሁሉ ሰብስቦ አንዱን ከሌላው ጋር በማወዳደር ይመርጣል የቋንቋን ጥራት ለመጠበቅ ከሚያስችሉትም ዘዴዎች ዋናው ክፍል ይኸው የቃላትን አመራረጥ ማወቅና የጥሩ ዐረፍተ ነገር አወቃቀር ይዘት ጭምር ነው ።

፬/ የቃላት መሣሪያነት

አንድ ተራ ሐናፂ እንኳ መላጊያ መሮ ፣ መጥረቢያና መጋዝ (ወዘተ) ሳይኖሩት ምንም ዓይነት ቅርፅ መሥራት አይችልም ። አንድ ጥሩ ደራሲም እንደዚሁ አንድ ሐሳብ ለማመንጨትና አቀራረቡም ስሜት የሚሰጥ እንዲሆን ለማድረግ ቃላት ዐረፍተ ነገሮችና መከፋፈያ አንቀጾች እንዲኖሩት ያስፈልጋል ። ለመሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም ብልሃት እንደሚያሻ ደራሲም ከተፈጥሮ ችሎታ ወይም ከልምድ የቀሠመውን ሐሳብ በቋንቋ መገናኛ ዘዴዎች ወደአንባቢያን ለማስተላለፍ የቃላትን መሣሪያነት አጠቃቀም የማወቅ ጥበብ (ቴክኒክ) እንዲኖረው ያስፈልጋል ።

በተለይም የአዲሱ ዘመን ደራስያንና የሊቃውንቱ ትልቅ ጥበብ ተብሎ የሚታመንበት ቁም ነገር እንደጉት ትኔ ሐሳብን ጨፍናና አፍና የሚይዝ የከባድ ቃላትን አጠቃቀም ወደጉን ትቶ ትርጉማቸው በቀላል የሚገኝ ግልጥነትና ውበት ያላቸውን ቃላት ባጫጭር ዐረፍተ ነገሮች ቀርፆ ስሜትን የሚቀሰቅሱ የሐሳብ ሥዕሎችን ለማቅረብ መቻል ነው ። በከባድ ቃላት የተጻፉ ድርሰቶችና የተዘረፉ ቅኔዎች የተደነገጉ ሕግጋትም ሆኑ የፍልስፍና ንድፈ ሐሳቦች በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት እያጡ ለዝክረ ነገር በየሙዚየሙና በአርኬ አብያተ መጻሕፍት ካልሆነ በቀር በብዙ ሕዝብ እጅ አይገኙም ። በቀላል ቃላት የተጻፉ ምርጥ መጻሕፍት ግን በማንኛውም ዐረፍተ ዘመን እንደከሩ ወግ ረግተው ሳይቆሙ እንደተገ እየታተሙ ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ ላይ ይገኛሉ ።

ግልጥነት ባላቸው ውብ ቃላትና በቀላል ዐረፍተ ነገር የተጻፉ ወይም የተነገሩ ቅኔዎችም ቃል በቃል እየተወራረሡ ብዙ መቶ ዓመታትን አቋርጠው ከአንዱ ትውልድ ወደሌላው እየተላለፉ ሲደነቁ ይኖራሉ ። በግጥምም ይሁን ወይም በሥዕላዊ የንግግር ጥበብተሽላልመው የተነገሩ ቃላት የተሸከሙት ሐሳብ እንደማር ወለላ ልዩ ጣዕምና ምርቃና ያለው ሆኖ ሲገኝ እንኳን የብሱን ውቅያኖስንም አቋርጦ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያስተጋባ ድምፅ ይኖራቸዋል ። በቀላሉም ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው መተርጐም ስለሚችሉ በየትኛውም ዐለም (አህጉር) ሲነገሩ ይኖራሉ ።

ቆስ መከብብ አጥናው

(ይቀጥላል)



www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ



የታዴዎስ የመጀመሪያ ስሙ ልብድዮስ ነበር ትርጓሜውም ልብደ ሠሪ ዓሣ ወጋሪ (ዓሣ እጥማጅ) ማለት ነው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ታዴዎስ ማለት ዘርና ማዕረር ማለት ነው ጧት ስንዴ ዘርቶ ለሠርክ መሥዋዕት አድርሷልና ታዴዎስ ቁጥሩ በመጀመሪያ ከተመረጡት ፲፪ ሐዋርያት ነው ።

ሐዋርያት ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት ሳይለያዩ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት እየተጠባበቁ ሳሉ ከዕርገቱ በኋላ ፲ ቀን ሲሞላ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸውና በማያውቁት ቋንቋ ሁሉ የመናገር ጸጋ ተሰጣቸው ፈሪዎች የነበሩ ደፋሮች ሆኑ ከብሉት ታደሱ ፤ አንድ ቋንቋ ብቻ ያውቁ የነበሩ ፸፪ ቋንቋዎች ተገልጸውላቸው በማንኛውም ቋንቋ ይናገሩ ጀመር ።

ከዚያ በኋላ የወንጌል ትምህርትን በሰፊው ለማሰራጨት እንዲችሉ ይህንን ዓለም በዕጣ ተካፈሉ ፤ በዚህ ጊዜ ለሐዋርያው ታዴዎስ በዕጣ ሶርያ ደርሶታል፤ በዕጣ ወደ ደረሰው ሀገር ለመሄድ ሲነሣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልኩ በአግረ ወጣት አምሳል ተገልጾ ሰላምታ ከሰጠው በኋላ ታዴዎስ ሆይ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ወደምትሄድበት ሀገር ሁሉ አትፍራ አትደንግጥ አይዞህ ብሎ አደፋፍሮት ሲያበቃ ወደ ሰማይ ዓርጓል ።

"ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው" ተብሎ እንደተጻፈው ከሐዋርያው ታዴዎስ ጋርም የተላከው ሐዋርያው ጴጥሮስ ነው ወደ ሶርያ ከተማ ለመግባት ሲቃረቡ አንድ አረጋዊ በሮችን ጠምዶ ሲያርስ ተመለከቱ በዚያ ሽማግሌ ገበሬ የሀገሩን ሕዝብ ጠባይ ለመረዳት እንደሚቻሉ በማመን ሐዋርያው ታዴዎስ ወደ ገበሬው ቀረብ አለና ከዚህ የሚበላ ምግብ አለህን ብሎ ጠየቀው ገበሬውም ከዚህ የሚበላ ምግብ የለኝም ነገር ግን በሮቼን እየጠበቃችሁ ቆዩኝ ወደ ቤቴ ሂጀ ምግብ አመጣላችኋለሁ አላቸው እነርሱም እሺ ብለው በአሳቡ ስለተስማሙ ገበሬው ምግብ ለማምጣት ወደ ቤቱ ሄደ ።

ታዴዎስ የሚያርሰውን ገበሬ ሥራ አስፈትተን ልከን የልመና በሮቹን ማቦዘን አይገባንም አለና እርፉን ይዞ በሮቹን መንዳት ሲጀምር ጴጥሮስ በእንቅብ የነበረውን የሥንዴ ዘር ባረከና ይዘራለት ጀመር ታዴዎስ በማረስ ጴጥሮስ በመዝራት አረጋዊው ገበሬ እስከ ሚመለስ ድረስ ፴ ትልም ዘርተው አረሱ የታረሰውም ወዲያውኑ በቅሎ አፈራ ። *

ሽማግሌውም ገበሬ ምግቡን አዘጋጅቶ ይዞ ቢመለስ እርሻው በመላ ታርሶ ተዘርቶ የተዘራውም አፍርቶ ስላገኘው በጣም ተደሰተ ተደነቀም ወዲያው ከእነ ታዴዎስ እግር በታች ወድቆ እናንተ ከሰማይ የወረዳችሁ እውነተኞች አማልክት ናችሁ አላቸው እነርሱም እኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ታዛዦች ነን እንጅ አማልክት አይደለንም አሉት ፤ ገበሬውም ይህንን አስደናቂና አስደሳች ሥራ ስለሠራችሁልኝ ልከተላችሁ ወደምትሄዱበትም ቦታ አብሬ እየሄድኩ ያዘዛችሁኝን ሁሉ እፈጽማለሁ ብሎ ከእግራቸው በታች ወድቆ ለመናቸው ።

እነታዴዎስ ግን አሁን እኛን ተከትለህ መሄድ አይገባህም ወደቤትህ ተመለስና የለመንካቸውን በሮች ለባለቤታቸው ስጥ ሚስትህም ልጆችህም ቤተሰቦችህም በጠቅላላ ያለህበትን ማወቅ ይገባቸዋል ስለዚህ ወደቤትህ ሂድና ምግብ አዘጋጅ ለማስተማር የመጣን ስለሆነ በዚህ ሀገር እንሰነብታለን ከአንተም ቤት ምግብ እንመገባለን አሉት ።

አረጋዊው ገበሬ በንግግሩ ተደስቶ እሸቱን ከበሬ ዕቃው ጋር አነባብሮ በትከሻው ላይ ተሸክሞ በሮቹን እየነዳ ወደ ቤቱ ተመለሰ ያለ ወቅቱ በተአምር ያፈራውን የስንዴ እሸት ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሲገባ የተመለከቱ ሁሉ እጅግ በጣም ተገረሙ በጉዳዩ የተገረሙ ሰዎች ወደ እርሱ ሄደው ይህንን እሸት ከወዴት አመጣኸው ? ጊዜው የዘር ወራት እንጂ የመከር ወራት አይደለም አሉት ።

አራሹ ገበሬ ግን ከደስታው ብዛት የተነሣ መልስ ሊሰጣቸው አልፈለገም ፤ በመጀመሪያ የለመናቸውን በሬዎች ለባለቤቱ ሰጠና ለእነታዴዎስ ግብዣውን ያዘጋጅ ጀመር ጉዳዩ በሀገሩ ሁሉ ስለተሰራጨ ከሕዝቡ የተውጣጡ ሰዎች ሂደው ይህንን እሸት ከወዴት እንዳመጣኸው ንገረን ካልነገርከን ግን እንገድልሃለን ብለው አስፈራሩት ገበሬውም ለሕይወቱ ስለፈራ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻ ድረስ አንድ ነገር ሳይደብቅ ግልጽ አድርጎ ነገራቸው እነርሱም ይህንን አስደናቂ ተአምር ያደረጉትን ሰዎች አሳየን ብለው መልሰው ስለጠየቁት ጥቂት ጊዜ ታገሡ ለግብዣ ወደ እኔ ቤት ስለሚመጡ ያን ጊዜ ታዩአቸዋላችሁ አላቸው ።

እነርሱ ግን እነዚህ ሰዎች ከ፲፪ ሐዋርያት መሠረያን እንደሆኑ ወቀልን ስለዚህ አሁኑኑ ተነሡና ወደአሉበት ሄደን ሳያስቡት በድንገት ደርሰን እንግደላቸው በማለት ይመካከሩ ጀመር ከመካከላቸው አንዳንድ ደግሞ ልንገድላቸው አንችልም እነዚህን ሰዎች ኢየሱስ የሚሉት አምላካቸው ይረዳቸዋል የፈለጉትንም ሁሉ ያደርግላቸዋል አሉ ።

ከዚያ በኋላ እነታዴዎስ ወደ ከተማ ገብተው የወንጌልን ቃል በሰፊው ያስተምሩ ጀመር በተለይ ሐዋርያ ታዴዎስ የሕዝቡ ልቡና ወደ አእምሮተ እግዚአብሔር እንዲለወጥ ወደ ፈጣሪው ቢጸልይ በሕዝቡ ላይ የነበረው መንፈስ ሰይጣን ተባረረና ሕዝቡ በእግዚአብሔር አምነው ተጠመቁ በዚያው ሐዋርያው ድውያንን ፈውሷል የዕውራንን ዓይን አብርቷል ለምጻሞችን አንጽቷል ደንቆሮች እንዲሰሙ ዲዳዎች እንዲናገሩ አንካሶች በትክክል እንዲራመዱ ከማድረጉም ሌላ አጋንንትን ከሰዎች አስወጥቶ አባሯል ሙታንንም አስነሥቷል ሐዋርያው ታዴዎስ በዚያ ሀገር የፈጸመው ገቢረ ተአምር ይህ ብቻ አይደለም ከዕለታት አንድ ቀን ብዙ ሰዎችን ሰብስቦ "እውነት እውነት እላችኋለሁ ለባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል ከነጭነቱ በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል" እያለ ሲያስተምር አንድ ባለጸጋ ወጣት ሰምቶ እድን ዘንድ ምን ላድርግ ሲል ታዴዎስን ጠየቀው ሐዋርያውም ያለህን ገንዘብ ሁሉ ለድሃ ስጥ ትድናለህ ስላለው ባለጸጋው በጣም ተናደደና ዘሎ አንገቱን ለማነቅ ታገለው ታዴዎስ ግን ምንም ሳይደነግጥ ትምህርቱን በመቀጠል ላይ ሳለ ግመል የሜኒ ነጋዴ በፊቱ አለፈ ሕዝቡም በቃል ያስተማርከንን በግብር ገለጽህ አሳየን አሉት ።

ሐዋርያው መርፌ እየሠራ የሚሸጥ ወዳጅ ስለነበረው መርፌ ሠርተህ ላክልኝ ብሎ ላከበት እርሱም ያገዘኩት መስሎት የመርፌውን ቀዳዳ ሰፊ አድርጎ ሠርቶ ላከለት ታዴዎስም እንደማነኛውም መርፌ አድርጎ ሠርቶ እንዲልክለት መልእክተኛ ላከበት እርሱም እንደተራ መርፌ አድርጎ ሠርቶ ላከለት ።

ሐዋርያው ታዴዎስ በትምህርተ መስቀል አማትቦ ከጸለየ በኋላ ግመሉን ከእንጭኑቱና ከእነባለቤቱ በመርፌው ቀዳዳ ውስጥ እንድታልፍ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዝሃለሁ አለና ሶስት ጊዜያት መላልሶ አሳልፎ ለተሰበሰቡት ሕዝቦች እንዳሣያቸው ተጽፎአል ።

ከዚያ በኋላ ወጣቱ ባለጸጋ በሐዋርያ ታዴዎስ እግር በታች ወድቆ ይቅርታ ጠይቆ በታዴዎስ አምላክ አምና ተጠምቋል እርሱ ብቻ ሳይሆን የሐዋርያውን ትምህርት የሰሙና ተአምራቱንም የተመለከቱ ሁሉ በጠቅላላ በክርስቶስ ስም አምነው ተጠምቀዋል ሐዋርያው ታዴዎስ በሶርያ በአርመን በሚስጶታሚያና በሌሎችም አህጉር እየተዘዋወረ ወንጌልን አስተምሮ በመጨረሻ ፀረ ወንጌል የሆኑ አረማውያን ሐምሌ ሁለት ቀን በገመድ አንቀው ገድለውታል ። በዚህም ዕለት ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያውን በሚገባ ታስታውሰዋለች ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያነትን ሲልክ እኔ እንደበጐች በተኩሎች መካከል እልካችኋለሁና እንደ ዕባብ ብልሆች እንደርግብ የዋሆች ሁኑ ሥጋን የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይችሉትን አትፍሩ የሚለውን ትእዛዝ መመሪያ በማድረግ ሐዋርያው ታዴዎስ ለትምህርተ ወንጌል በመሰማራቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን አስተምሮ አሳምኖ አጥምቆ የክርስቶስ ወገኖች ከማድረጉም ሌላ ብዙ ድውያንንም መፈወሱ ከላይ ተገልጿል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ማንም ከእነዚህ ከተናናሾች ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም" ብሎ በተናገረው መሠረት ሐዋርያ ታዴዎስ በእግዚአብሔር አምና በጸሎቱ ተማጽና ዝክሩን ለሚዘክር መተሰቢያውን ለሚያደርግ መጽሐፈ ገድሉን ለሚጽፍና ለሚያጽፍ ለሚያነብና ለሚሰማ ሁሉ ዋጋውን መንግሥተ ሰማያትን እንደሚያገኝ ቃል ኪዳን ከፈጣሪው ተቀብሏል ስለዚህ የሐዋርያትን ረድኤትና በረከት ከእግዚአብሔር ለመቀበል መታሰቢያቸውን ማድረግ የማንኛውም ክርስቲያን ተግባር ነው ።

ገድለ ሐዋርያት ገጽ ፪፻ ፺፯ ስንክሣር ሐምሌ ፪ ቀን ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

---

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከገጽ ፳፩ የዞረ

እኛም በአጠቃላይ እንደተረዳነው የሸዋ ሀገረ ስብከት ትምህርትን ከልማት ጋር በማጣመር የጉጂ እንዱስትሪን ለማቋቋምና የተቋቋመውን ለማጠናከር ባለው የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዱ ምሳሌ የሚሆኑ ሥራዎችን አሳይቶአል። በአቃቂ የተቋቋመው የጉጂ እንዱስትሪም ቀደም ሲል በ፴ ብር ይሰቃይ የነበረውን ካህን ወደ ሁለት መቶ ብር አድርሶት መታየቱ በዚህ ዓይነቱ ሥራ ላልተደራጁ ካህናት የሚያነቃቃ ነው። ይህ የካህናት የኀብረት ሥራ በአንድ ዓመት ዕድሜ ከወጭ ቀሪ ሰባት ሺ ተቀማጭ ማግኘቱም ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መልካም አርአያ ነው በርቱ እንላለን ።

በለጠ አበበ

---



* ፩. ታዴዎስ፣ ቀ፣ ታ፲ ክሎ፣ ፋ ሀርስ፣ ገራህተ፣
፪. ወጴጥሮስ፣ ዘርአ፣ ሠጎስ፣ ፲ ሽታልምተ፡፡
፫. ሬረየ፣ ስሬሃ፣ ወኅን፣ ለዩተ፣

www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሕይወት ላይ ምን አነበብን?

## ወደፊትስ ....?

በዚህ ወርኃዊ መጽሔት ዜና ሊቃውንት የተባለው ይህ አምድ ከተከፈተበት ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊት ጀምሮ አርባ የሚሆኑ የኢትዮጵያ ታላላቅ ሊቃውንት የሕይወት ታሪክ ተተንትኗል ።

ይህንኑ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት የተደረገውም በረጅም ጊዜ ትምህርት በምርምር በማስተማር በሥነ ጽሑፍ በመጥምተ ርዕስ ፣ በምናኔ ፣ በአስተዳደርና በፍርድ አሰጣጥ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ መንግሥት ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱትን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ከዘመኑ ትውልድ ጋር በታሪክ ለማስተዋወቅ ነው ።

ሕይወታቸውን በሥራ ያስጌጡትና ኢትዮጵያን በታሪክ ልዩ ልዩ ተግባር ፍሬያማ ውጤት እንድታበረክት በማድረግ ከልብ የደከሙት ታታሪዎች ሊቃውንት ታሪክ ያለው አይሞትም የሚለውን የአበው ምሳሌ ተግባራዊ ከማድረጋቸውም አንጻር ምሳሌነታቸው ለአሁኑም ሆነ ለተተኪው ትውልድ የሚጠቅም መሆኑን ለመገምገም አያዳግትም ።

በመጽሔቱ ዝክረ ነገራቸው ከተገለጸው ታላላቅ ሊቃውንት መካከል በይበልጥ በሥራና በታሪክ ሚዛን ትኩረት የምንሰጣቸው ለእነማን ነው? ብለን የጠየቅን እንደሆነ ሰማኒያ የሚሆኑትን ደቀ መዛሙርት በትምህርት የወለዱትን ፣ ከማስተማር ጉባኤ በቀር የሹመት ስሙ ከፊቴ አይነግብኝ ያሉትን በደብረ ታቦር የሃይማኖት ጉባኤም “ምንት ይእቲ ቁስጥንጥንያ ፡ ወኒቅያ ደብረ ታቦር ነያ ቁስጥንጥንያ ምንድናት? ደብረ ታቦርም ኒቅያ ናት” ብለው በደቂቃ ጊዜ ውስጥ የዘረፉ ቅኔ ያካሔዱትን የአራቱን ጉባኤያት ከፍተኛ ሊቅ አራት ዓይና ጐሹን በዓይነ ሕሊና እንመለከታቸዋለን ።

የአባቶችን የምርምርና የትርጓሜ ስልት ለዘመኑና ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ በዘመናዊ ማኅተም ለማባዛት በተደረገው ጥረትም ከሌሎች ሊቃውንት ጋር ሆነው በትምህርት የወረሱትን የአራቱን ወንጌላት ትርጉም ያበረከቱትንና ከመጻሕፍተ ሊቃውንትም በተጨማሪ የቅዱስ ቁርሎስን መጽሐፍ ትርጉም ለማኅተም ያቀረቡትን አለቃ ኀሩይ ፈንታን የአሥራ አራቱን ቅዳሴያት ትርጉም አቅርበው ያሳተሙትን መምህር ገሪማን (በኋላ ብፁዕ አቡነ ሚካኤልን) አርባ ስድስቱን መጻሕፍተ ብሉያት ከሌሎች ሊቃውንት ጋር ሆነውና ከመምህራን በትምህርት እንደወረሱት አድርገው በአንድምታ ትርጉም እንዲታተም በማለት ጽሑፉን ያበረከቱትን የአራቱን ጉባዔ ሊቅ መምህር ፈላታዎስን

በሕንድና በግብጽ በሌሎችም የውጭ አገሮች ተዘዋውረውና ልዩ ልዩ የሆኑ ቋንቋዎችን አጥንተው መጽሐፍ ቅዱስን በተጣራ ሁኔታ ወደ አማርኛ ተርጉመው እንዲታተም ያደረጉትን አባ ሮሜን ወይም አባ አብርሃምን በማይሞተው ታሪካቸው አንጻር ሆነን ሕያው ሥራቸውን ወደኋላ ተመልሰን እየተመለከትን ወደፊትም በዚህ ዓይነቱ ተግባራዊ ይዘት የሚተኩ ሊቃውንት ይኖሩ ዘንድ የቤተ ክርስቲያን ት/ቤቶች መጠናከር ይኖርባቸዋል ።

የሊቃውንት ከፍተኛ ተግባራዊ ውጤት በሆነው በድርሰትና በሥነ ጽሑፍ ዓለም ውስጥ ከተሠማሩትም ሊቃውንት በግዕዝ በዕዝል በዓራራይ ማለት ሦስት ዓይነት ጣዕመ ዜማ ያለበትን የጾም ድጓ መዝገብ ድጓ ዝማሬና መዋሥዕት የደረሰውንና በጽሑፍ ያስተላለፈውን ኢትዮጵያዊውን ቅዱስ ያሬድን በተለያዩ የውጭ አገሮች የታወቁና ፯ ያህል ልዩ ልዩ ድርሰቶች ደርሰው በጽሑፍ ያበረከቱትን የጋስጫውን አባ ጊዮርጊስን በዚህ ዓይነቱ ሥራ ተባባሪዎች የሆኑትን ዓቃቤ ሰዓት ክብቴንና አለቃ ደስታ እሸቴን አሥራ ስምንት የሆኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ደርሰው እንዲሁም የኢትዮጵያ ሊቃውንት ቅኔዎች በቁጥር አንድ ሙቶ አሥር የሚሆኑትን ሰብስበው በሌሎችም ስለስብሰባው ተረድተው ራሳቸው ያሳተሙትን ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን የመሳሰሉትንም ሁሉ ከልብ እናስባቸዋለን ።

መንግሥታዊ በሆነው የሥራ ድርሻ ረገድም በፍርድ ባለሥልጣኖች ልዩ ልዩ የሆነ የወንጀል ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የፍትሐ ነገሥቱን መጽሐፍ በአደባባይ ዘርግተው ተፈላጊውን አንቀጽ አውጥተውና ስለዋናው የመጨረሻ ባለሥልጣን ሆነው ያስተላለፉት በነበረው ፍትሕ ሕጋዊ (ሥጋዊ ፍርድ በጐንደር መንግሥት የነበሩትን ዓቃቤ ሰዓት ክብቴን በዓፄ ዮሐንስ ዘመን በጣም የታወቁትን ሊቁ መርዓዊን በዓፄ ምኒልክና በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስንና ሊቁ ገብረ ክርስቶስን መልአከ ገነት ጽጌ ሻውልን በመንፈሳዊው ተግባራቸው አንጻር ስለ ሥጋዊው አስተዳደር ለአገራቸው ስለ አበረከቱት አስተዋጽኦ የታሪክ አቋማቸውን አረጋግጠዋል ።

ስለ ትርጓሜ መጻሕፍት መቃናት በየጊዜው በተደረገው ምርምርና ሥልት ዓይነ ሥውሩ መምህር ኤስድሮስ የቀድሞው የላይ ቤት የሐዲስ ትርጓሜ ዝብዝብ ይበዛዋል በማለት በጣና ደሴት ተገኝተው እንደጊዜው ሁኔታ በአንባቢና በመሪ እየተረዱ ትርጓሜ ሐዲሳትን አንድ በአንድ አሻሽለው የታች ቤት ትርጓሜ በማሰኘታቸውና በዚህ ሥራቸው ውጤታቸውን በትምህርት የተከታተሉት ብዙዎች ሊቃውንት አድንቀዋቸዋል ። የላይ ቤትን ትርጓሜ ቀደም ብለው የተማሩትም ሊቃውንት እነ መምህር አካለ ወልድ ሠርፀ ወልድና እነ መምህር ወልደ ሚካኤል ኃይሌ ሳይቀሩ የሐዲስ ትርጓሜ ትምህርታቸው በመምህር ኤስድሮስ የታች ቤት ትርጓሜ እንዲሻሻል አድርገዋል ።

የምርምር ሂደታቸውን ለማጠናከር ልዩ ልዩ የውጭ አገሮችን ቋንቋ ከተከታተሉትና ካጠኑት መካከል ከላይ እንደተገለጸው አባ ሮሜ ወይም አባ አብርሃምን ከአራቱ ጉባኤያት ትምህርት ችሎታቸው ሌላ የዓረብኛ ቋንቋ በሚገባ አድርገው ያጠኑትን ሊቁን ወልደ አብን (ወልደ አብ ወልደ ሚካኤልን) በእንግሊዝኛ በሳይንስ ሞያ ይደነቁ የነበሩትን አለቃ ደስታ እንግዳን የመሳሰሉትንም ሁሉ ብዙዎች ያደንቁዋቸዋል ።

ሊቃውንቱ ስለሀገር ፍቅርና ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት በነበራቸው ዝንባሌም ኢትዮጵያ በጠላት በተወረረችበት ጊዜ በዜና ማርቆስ ገዳም በግፍዕ ተደብድበው የሞቱትን መምህር ወልደ ሚካኤልን በኢሉባቦር ሀገረ ስብከታቸው የሰማዕትነት ክብር የተቀበሉትን ብፁዕ አቡነ ሚካኤልን በሚያሳዝን ሁኔታ የተገደሉትን መምህር በላይ አፈስኩን የዛሬውም ሆነ የሚተካው ትውልድ ሊያስባቸው ይኖራል ።

ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መካከል ብዙዎቹ በጉባኤ በማስተማር ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ጋር በድንግልና ሕይወት የመኖር ስሜት ስለሚያደርስባቸው እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ ድንግልናቸውን አክብረው ጠብቀው ከኖሩት ለምሳሌ ያህል መምህር አካለወልድን አለቃ ኅሩይ ፋንታን የአራቱን ጉባኤያት መምህርና የቅኔው ባለቤት የነበረውን ክፍለ ዮሐንስን የአሰቦትን ገዳም ያስተዳድሩ የነበሩትን አለቃ ገብረ መድኅንን ፣ መምህር ወልደ ጊዮርጊስን እንጠቅሳቸዋለን ።

ብራና ዳምጦ ብሔራዊ ቀለም ቀምሞና ቀለም ቀንድ ቀርጾ ቁም ጽሕፈት በመጻፍ በኩልም ከላይ የተጠቀሰው ክፍለ ዮሐንስ መልአከ ፀሐይ ተገኝ መልአከ ብርሃን ፋንታ ገብርዬ ከላይ የተጻፉት አለቃ ደስታ እንግዳ አለቃ ደስታ እሸቴ ምሳሌዎች ሆነው የሚቀርቡ ናቸው ፤ በተለይ ደግሞ መልአከ ፀሐይ ተገኝ ስለቤተ ክርስቲያንና ታላላቅ ቤቶች ሥራ ፕላን በመስጠትና ልዩ ልዩ የሥራ ዕቅዶችን በማውጣት የታወቁ ስለሆኑ መልአከ ብርሃን ፋንታ ገብርዬም በተጨማሪ በድጉሠት ሥዕልን በመሣል ሐረግን በመንደፍና በገናን በመደርደር ረገድ ስመ ጥሩ ነበሩ ።

ሊቃውንቱ ከዚህ ሁሉ በላይ ያገር ውስጥ ፀጥታ እንዲጠበቅ የእርስ በርስ ደም በከንቱ እንዳይፈስ የሰላም ጓዶች እንደነበሩ ታሪክ ምስክር ነው ። ለመረጃም ያህል ዓፄ ዮሐንስንና ዓፄ ምኒልክን (በዚያን ጊዜ ንጉሥ ምኒልክን) በማስታረቅ የወንድማማች ሕይወት እንዳይጠፋና ፀጥታ እንዳይቃወስ ያደረጉትን መምህር አካለ ወልድን አለቃ ምላትን ብንጠቅሳቸው በቂ ነው የኢትዮጵያን ሊቃውንት እጅግ በሚያስመሰግናቸው በቅኔ ችሎታ ረገድም የሙያን መድረክ የያዙት ብዙዎች ስለሆኑ መዘርዘር የተወሰነውን ገጽ ያጣብበዋል ።

### እንዲህ ከሆነ ሊቃውንቱን ምን ዓይነት የሥራ ዕቅድና የትምህርት መርሐ ግብር ጐደላቸው?

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደተዘረዘረው ሁሉ በትምህርት በማስተማር በሥነ ጽሑፍ በልዩ ልዩ የቅኔ ፈጠራ በተግባረ እድ በመሳሰለው ሁሉ ባበረከቱት አስተዋጽኦ ታሪክ እጁን ዘርግቶ ወደ መድረኩ አቅርቦዋቸዋል ። ይሁን እንጂ አበው “በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል” ያሉትን ባለመከተል አንዳንዶቹ ሊቃውንት የሥነ ጽሑፍ አቋም ያልተከተሉ መሆኑ ታውቋል ።

እንዲያውም በሥነ ጽሑፍ ዓለም ውስጥ ማንፀባረቃቸው ቀርቶ ስማቸውን ለመጻፍ የሚቸገሩ እንደነበሩ የጆሮ ብቻ ሳይሆን የዐይን ምስክሮችን ለመቁጠር ይቻላል ። በመሆኑም እንዲህ ያሉት ሁሉ ሞያቸውን ምርመራቸውን ማለትም ጠቅላላ ዕውቀታቸውን በቃል ለቀረቡዋቸው ሰዎች ከማስተላለፍ ይልቅ ለታሪክና ለትውልድ በሚቆየው ሥነ ጽሑፍ ማራባቱ ለሥራ ሰውነታቸው የበለጠ ሞገስ ያተርፍላት ነበር ይህ ባለመሆኑ ግን በሊቃውንቱ የቁጥር ብዛት አንጻር ሥነ ጽሑፎችን በከፍተኛ ደረጃ ለመገምገም አልቻልንም።

ሊቃውንቱ ያስተማሩዋቸው ደቀ መዛሙርት በሞት ተለይተዋል የማይሞተውም ሥነ ጽሑፍ ከአካባቢያቸው ርቋል ታዲያ በምን እናስታውሳቸው? ዛሬ ያሉትም ቢሆኑ የሥነ ጽሑፍን ፈለግ ካልተከተሉና ለዛሬውና ለነገው ትውልድ የሚተላለፍ የዕውቀትና የምርምር ቅርስ በጽሑፍ ካላስተላለፉ ወቀሳው የሚዝላቸው አይመስልም ።

“ሰርቫንትስ” የተባለው የሥነ ጽሑፍ ሰው “ብርዕ የአእምሮ ምላስ ነው” ብሏልና ።

ከዚህም ሌላ የሚያጠያይቀን ነገር ይኖራል ይኸውም ስለትርጓሜ መጻሕፍት አወራረድና ይዘት ነው ።

በመሠረቱ መጻሕፍትን ማን ተረጐማቸው? መልሱ ሊቃውንት ናቸው የሚል መሆኑ አያጠራጥርም በአንድ ዓረፍተ ነገር ለተወሰነ ምንባብ የሚሰጠው የትርጓሜ ሥልት ወይም አወራረድ ከደራሲው ወይም ከመሠረታዊው መምህር ግዕዛዊ ንባብ በላይ ስለምን በአንድምታ ትርጉም ተራዘመ? ሲባል ንባቡን ለማመሥጠር ወይም ውስጠ ምሥጢሩን ለማስረዳት ነው የሚል መልስ እንደሚቀርብ እሙን ነው ።

ሌላም አጠያያቂ ሁኔታ አለ ሊቃውንት ከየአስተማሪዎቻቸው በጉባኤ በተላለፈላቸው አማርኛ ብቻ እንዲማሩ ፤ ሲያስተምሩም ያንኑ የተማሩትን ብቻ ጠብቀውና ተጠንቅቀው ለማስተላለፍ ይጠነቀቃሉ አደራም ይኖርባቸዋል ለ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ

## ትምህርት ፷

# የግእዝ ትምህርት

| | |
|---|---|
| እንተ | የ |
| እለ | ” |
| ዘ | ” |
| በእንተ | ስለ |

## መክሥት

"እለ እንተ ዘ በአንቀጽ ላይ ሲወድቁ ቅጽልነትን ያሳያሉ ። በስም ላይ ሲወድቁ ደግሞ ዘርፍ አያያዥ አገናዛቢ ይሆናሉ ። በራሳቸው ሲነገሩ ግን የእርባታ መሪዎችን እየተከተሉ ባለገንዘብነትን ያሳያሉ ። ሲረቡም መድረሻ ፊደላቸውን ወደሣልስነት ይለውጡና "አ" የሚል ባዕድ ፊደል ይጨምራሉ ።

ምሳሌ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩. ዚአየ | የእኔ | ዚአነ | የእኛ |
| ዚአከ | የአንተ | ዚአክሙ ተባ/ | የእናንተ |
| ዚአኪ | የአንቺ | ዚአክን/አን/ | ” |
| ዚአሃ | የእርስዋ | ዚአሆን/አን/ | የእነርሱ |
| ዚአሁ | የእርሱ | ዚአሆሙ/ተባ/ | ” |
| ፪. እንቲአየ | የእኔ | እንቲአነ | የእኛ |
| እንቲአከ | የአንተ | እንቲአክሙ/ተባ/ | የእናንተ |
| እንቲአኪ | የአንቺ | እንቲአክን አን/ | የእናንተ |
| እንቲአሁ | የእርሱ | እንቲአሆሙ/ተባ/ | የእነርሱ |
| እንቲአሃ | የእርስዋ | እንቲአሆን/አን/ | የእነርሱ |
| ፫. እሊአየ | የእኔ | እሊአነ | የእኛ |
| እሊአከ | የአንተ | እሊአክሙ/ተባ/ | የእናንተ |
| እሊአኪ | የአንቺ | እሊአክን/አን/ | ” |
| እሊአሁ | የእርሱ | እሊአሆሙ | የእነርሱ |
| እሊአሃ | የእርስዋ | እሊአሆን/አን | » |

ከዚህ በላይ ባጠናነው የአገናዛቢ እርባታ ዐረፍተ ነገር ለመሥራት የሚከተሉትን ቃላት እናጥና ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ብርዕ | ብርዕ | አብራዕ | ብዕሮች |
| መዝገበ ቃል | የቃላት መፍቻ | መዛግብተ ቃል | የቃላት መፍቻዎች |
| መርሐ | መክፈቻ | መራሕት | መክፈቻዎች |
| ሠረገላ | መኪና | ሠገላት | መኪናዎች |
| ሑሴሚት | ድመት | | |

## ዐረፍተ ነገር

ዝንቱ ብርዕ ዚአየ ውእቱ
ዝኩ ሠረገላ ዚአከ ውእቱ
ዚአየ ውእቱ ዚአኪ
ዛቲ ሑሴሚት ዘመኑ ይእቲ
ዛቲ ሑሴሚት ይእቲ እንቲ አየ
ዚአከ ውእቱ መዝገበ ቃል
ዚአነ እሙንቱ ሠረገላት /ተባ/
እሊአየ እሙንቱ አባግዕ /ተባ/
እሊአኪ እማንቱ አባግዐት /አን/
እሉ መራሑት እሊአከ እሙንቱ

ይህ ብርዕ የእኔ ነው
ያ መኪና ያንተ ነው
የእኔ የአንቺ ነው
ይህቺ ድመት የማን ናት?
ይህቺ ድመት የእኔ ናት
የቃላት መፍቻው የአንተ ነው
መኪናዎቹየእኛ ናቸው
እነዚያ በጎች የእኔ ናቸው
እነዚያ በጎች ያንቺ ናቸው
እነዚህ መክፈቻዎች/ቁልፎች/ያንተናቸው

### ግብረ ቤት

"በእንተ" "እለ" የተሰኙትን ቃላት" ዘ" እና "እንተ" በተረቡበት ሕግ ለማርባት ሞክሩ ።



# ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድምአገኘሁ

### የወጣቶች ምስክርነት

ስለ ሃይማኖታቸው የሚመሰክሩና እስከ ሞት ድረስ የሚጋደሉ በእድሜ የበሰሉት ብቻ ሳይሆኑ ወጣቶችም ጭምር መሆን እንደሚገባቸው የታመነ ነው ። በዚህ መሠረት ነው ብዙዎች ወጣቶች እውነተኛውን ሃይማኖትና ትክክለኛውን የእግዚአብሔር መንገድ ለሰዎች እየገለጡና በአደባባይ እየመሰከሩ ያለፉት ።

የሕፃኑ ቂርቆስ መንፈሳዊ ተጋድሎና የሰማዕትነት ታሪክ እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚችል ታላቅ ምሳሌነት ያለው ነው

ቅዱስ ቂርቆስ በተወለደ በ፫ ዓመቱ ስላደረገው መንፈሳዊ ተጋድሎና የሰማዕትነት ተግባሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስሙ ጽላት ተቀርፆለት በአማላጅነቱ ታምኖበት ለዘለዓለም ሲከበር ይኖራል ።

ቂርቆስ የተወለደበት ዘመን መናፍቃን የበዙበትና ስለክርስቶስ የሚመሰክር ሁሉ በሞት እንዲቀጣ የሚደረግበት ወቅት በመሆኑ ለክርስቲያኖች እጅግ አሰቃቂ የሆነ የጭንቅ ጊዜ ነበር ከዚህም የተነሣ ብዙዎች ሰማዕታት በመጋዝ እየተሰነጠቁ በሰይፍ እየተቆረጡና በእሳት እየተቃጠሉ እንዲሞቱ ተደርጎ እንደነበር ከገድላቸው መማርና መረዳት ይቻላል ።

ሰማዕቱ ቂርቆስ ምንም እንኳን በእድሜ የሦስት ዓመት ሕፃን ቢሆንም የእግዚአብሔር ፀጋ ከእሱ ጋር ስለነበርና መንፈስ ቅዱስም ስለገለጠለት እንደ ዕድሜው ሕፃንነት ሳይሆን እንደታላቅ ባለአእምሮ ሰው ስለክርስቶስ በማስተማሩና የእግዚአብሔርን ምስጢር እየገለጠ በማስረዳት ተአምራታዊ የሆነ የምስክርነት ተግባር ሲያከናውን በመታየቱ በዘመኑ የነበሩ ፀረ ክርስትና የሆኑ ክፍሎች የክርስቶስ ቃል ለሕዝብ መዳረሱና እውነተኛው ሕገ ወንጌል መሰበኩ እጅግ ስላስቀናቸውና ስላበሳጫቸው ሰማዕቱ ቂርቆስ ይህንኑ መንፈሳዊ ተግባሩን እንዲያቆም ጠይቀውት እምቢ በማለቱ በጠላትነት ተነሡበትና በብርቱ ሊቀጡት ወሰኑ ። ነገር ግን እሱ በእምነቱ እየበረታና እየጠነከረ በመሄዱ በትምህርቱ ብዙ ተከታዮችን አፈራ እንጂ ከዓላማው ወደኋላ ሊል አልቻለም ። ስለዚህ እሱን መቀጣጫ አድርገው ሕዝቡን በማስፈራራት ዓላማውን ለማክሸፍ ሲሉ ከብረት የተሠራ ጋን በእሳት ላይ ጥደው ቂርቆስንና እናቱ ኢየሉጣን በዚያ ውስጥ ለመጨመርና በፍል ውኃ ተቀቅለው እንዲሞቱ ለማድረግ ወሰኑ።

ይህንን ለማድረግ በሚዘጋጁበት ጊዜ ቅድስት ኢየሉጣ ፈርታ ስትጨነቅ አይቶ "ጥብእኪ እም ወኢትፍርሂ" እናቴ ሆይ በእምነትሽ ጠንክሪ አትጠራጠሪ ብሎ ካጽናናት በኋላ በብረቱ ጋን በፈላው ውኃ ውስጥ ከእናቱ ጋር ሲጨምሩት ሞትን በመናቅ ምስክርነቱን ሳያቋርጥ እስከ መጨረሻው ተጋድሏል።

በቅዱስ ቂርቆስና በእናቱ በቅድስት ኢየሉጣ ላይ የደረሰውን የፈተና ክብደትና የእምነታቸውን ጽናት የተመለከተ እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ እሳቱንና ፍል ውኃውን አቀዝቅዞ በቅዱስ ቂርቆስም ሆነ በእናቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባቸው ሊድኑ ችለዋል ። በነሱ ላይ የሆነውን ተአምራታዊ ድኅነት ካዩት ብዙዎች በቂርቆስና በኢየሉጣ አምላክ በእግዚአብሔር አምነዋል ። ሕፃኑ ቂርቆስ ባደረገው ተጋድሎና ገና በሕፃንነት ዕድሜው ስለክርስቶስ በሰጠው ዕውነተኛ ምስክርነት ስላሳየውም የእምነት ጽናት በቤተ ክርስቲያን ሰማዕት የሚል የቅድስና ስም ተሰጥቶት ከሌሎች ቅዱሳን ሰማዕታት ጋር በመቆጠሩ ከላይ እንደተጠቀሰው ጽላት ተቀርፆለት በስሙ በታነፁት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በየወሩ በ፲፱ኛው ቀን የመታሰቢያው በዓል ሲከበር ይኖራል ። በተለይም ሐምሌ ፲፱ ቀን በመከራ የተፈተነበትና በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት እሳቱ ጠፍቶ እሱና እናቱ ከእሳት ቃጠሎ ማለት በንፍር ውኃ ውስጥ ተቀቅለው ከመሞት የዳኑበት ዕለት በመሆኑ ይህ ቀን የቅዱስ ገብርኤልና የሰማዕቱ ቅዱስ ቂርቆስ ጽላት ባሉበት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በደማቅ ሁኔታ ሲከበር ይኖራል ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህ በዘመነ ሐዲስ የተፈጸመ ገድል ሲሆን በዘመነ ብሉይ (ኦሪት) ደግሞ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይና አስደናቂ የሆነ ሌላ መንፈሳዊ ታሪክ አለ ። እሱም የሠለስቱ ደቂቅ ጽኑ እምነትና ጥንካሬ እንዲሁም እግዚአብሔር በነሱ ላይ ያሳየው ተአምር ነው ቅዱስ ገብርኤልም ለወጣቶች የሚያደርገው ተራዳኢነት በቂርቆስ ተጋድሎ ጊዜ የተከሰተ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ለሠለስቱ ደቂቅም የተደረገ መሆኑ ነው ።

አናንያ ፣ አዛርያና ሚሳኤል ተብለው ይጠሩ የነበሩት እነዚህ ወጣቶች በፍጹም ልባቸውና አሳባቸው ፈጣሪያቸውን የሚያምኑ ነበሩ በዚያውም ላይ ጥበበኞችና አዋቂዎች በመሆናቸው በንጉሡ በናቡከደነፆር ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው ነበሩ ። ይህም ሆኖ ከንጉሡ ጋር በሥራ እንጂ በሃይማኖት አይተባበሩም ነበርና ከንጉሡ የታዘዘላቸውን ድርጎ እንኳ እንዳይበሉ ወስነው ጥራጥሬና ውኃ ብቻ ተመግበው መኖርን የመረጡ ናቸው ። ይህም ሲሆን ጣፋጭና ጥሩ ምግብ ከተመገቡት ሰዎች ይልቅ እነሱ አምረውና ወፍረው ታይተዋል ።

እነዚሁ ወጣቶች በጥበብና በማስተዋል የታወቁ በመሆናቸው ሲድራቅ ፣ ሚሳቅና አብደናጎ ተብለው ስማቸው ከመለወጡም ሌላ በንጉሡ ትእዛዝ በባቢሎን አውራጃ ተሾመው ሳሉ ንጉሡ ናቡከደነፆር ቁመቱ ፷ ክንድ ወርዱ ፯ ክንድ የሆነ የወርቅ ምስል አሠርቶ ማንኛውም ሰው በምረቃው በዓል ላይ እንዲገኝና ለምስሉ እንዲሰግድ አዋጅ አስነገረ ። በዚህም ምክንያት በዘመኑ የነበሩት መኳንንትና ሹማምንት እንዲሁም ተራው ሕዝብ ሁሉ እየመጡ ሲሰግዱ ሠለስቱ ደቂቅ ግን ወደዚያ ባለመምጣታቸውና ባለመስገዳቸው ተከሰው ወደንጉሡ ቀረቡ ።

ቀደም ሲል በወጣው አዋጅ መሠረት አለመምጣታቸውንና ለምስሉም አለመስገዳቸውን በድፍረት ስለተናገሩ ንጉሡ ተቆጥቶ አሁን ባትሰግዱና አምላኬን ባታመልኩ ወደ እቶን እሳት ትጣላላችሁ ከእጄስ የሚያድናችሁ ማነው? እያለ ቢያስፈራራቸውም "የምናመልከው እግዚአብሔር ከሚነደው እሳት ያድነናል ባያድነንም ላቆምከው ለወርቁ ምስል እንደማንሰግድ አማልክትህንም እንደማናመልክኸወቅ" በማለት ቁርጥ ያለ ውሳኔ በድፍረት ነገሩት ። በዚህ ጊዜ ቁጣው የበለጠ ገንፍሎ እሳቱ ከቀድሞ የበለጠ በጉድጓዱ ውስጥ ሰባት እጥፍ እንዲነድ አዞ እነዚያ ወጣቶች ከነልብሳቸው ታሥረው በእሳቱ ውስጥ እንዲቃጠሉ አስጥሏቸዋል በዚህም ከልክ በላይ ይነድ የነበረው እሳት በውስጡ ተጥለው የነበሩትን ወጣቶች ልብሳቸውን እንኳን ሳይነካው እነሱን ወደ እሳቱ የጣሏቸውን ገደለ ፣ የታሠሩበትንም ገመድ አቃጠለ በነሱ መካከልም ቅዱስ ገብርኤል ተገኝቶ ተረዳኤነቱን ገለጠ ። ትንቢት ዳንኤል ፩፡፩-፱ ፡ ፫፡፩.፴

ይህ ሊሆን የቻለው በወጣቶቹ እምነት በእግዚአብሔር አዳኝነት በቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት እንደሆነ የታመነ ነው ስለዚህ ወጣቶች ሁሉ ስለክርስቶስ መመስከርና ማስተማር ይኖርባቸዋል እምነታቸውም ጽኑዕ ሊሆን ይገባል

---

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ህን ንብረት አትመኝ " በሚለው መለኮታዊ ኃይለ ቃል በማሸነፍ ይህን መልካም ምሳሌነት ያለውን ግብር ለመፈጸም ችሏል ።

እኛም ይህንን የወታደሩን መልካም አድራጐት ስለሰማን ከባለንብረቷ ዘንድ ሄደን ሁኔታውን ለማጣራት ስለፈለግን ፲፱/፯/፹፬ ዓ.ም ቢታቸው ድረስ ሄደን ጠይቀን የሰጡን የማረጋገጫ ቃል ከዚህ በታች አቅርበናል ።

መጋቢት ፲፱ ቀን ፹፬ዓ.ም እኔ እመት ብዙነሽ ወልደየስ ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም የጥምቀትን በዓል ለማክበር ወደ ባሕረ ጥምቀት ወርጄ ሣለሁ ግምቱ ፮፻ (ስድስት መቶ)ብር የሆነ የእጅ ካቴና ወርቅ ከእጄ ላይ ወልቆ ወድቆ ሳለ እኔ መውደቁን ሣላውቅ አልፌ ከሄድኩ በኋላ ወ/ር አሻግሬ የተባለው ደግ ሰው ከኋላዬ ጠርቶ በማሣየት የወደቀውን ንብረቴን አንስቼ እንድወስድ ስለነገረኝ የእጅ ወርቄን ያለ እንከን ከመሬት አንስቼ ከእጄ አግብቼዋለሁ ስለዚህ ይህ ወታደር የተባረከ ስለሆነ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ይጠብቀው እላለሁ ሲሉ እውነተኛ ቃላቸውን ሰጥተው ፈርመዋል ።

እዚህ ላይ ይህን የመሰለ ዋጋው የበዛ ወርቅ ወድቆ ስታገኝ ሰውነትህ ሳይሣሣ እንዴት ጨክነህ ለባለንብረቷ ልትናገር ቻልክ ብለን ላቀረብንለት ጥያቄ ወ/ር አሻግሬ የሰጠን መልስ "ክርስቲያን ነኝ በምሥራቅ ጦር ግንባር ብዙ ተዋግቼአለሁ ተመትቼም ቆስዬ ብዙ ደም ፈሶኛል ነገር ግን ሕይወቴን አምላክ አተረፈኝ ስለዚህም የሰውን ገንዘብ አልፈልግም በዚህ ላይ ገንዘብን እኔ አገዝዘበታለሁ እንጅ እሱ እያገዝዝብኝም ባልደከምኩበት ገንዘብ መጠቀምንም አልፈልግም የራስ ባልሆነ ሀብት መጠቀም እንደማይገባም ተምሬአለሁ " ሲል ቃሉን ሰጥቶናል ።

እኛም የዚህ ወታደር አድራጐት ለሌሎች ትምህርት ይሆናል ብለን ስለአመን በትንሣኤ መጽሔት ቢወጣና ሰዎች ቢያነቡት መልካም መስሎ ስለታየን ልከነዋል ።

ማኅተም በሲዳሞ ክፍለ ሀገር የቦረና
አውራጃ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት
"ኢትዮጵያ ሥጋችን
ቤተክርስቲያን ነፍሳችን"
ፊርማ መምህር ኃይለ ማርያም መሸሻ



www.ethiopianorthodox.org

## "በኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ"

"በኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ ተከታዮቼን ግን አትንኩ"የሚለውንቃለ ምዕዳን ለገዳዮቻቸው ፈሽስቶች ያስተላለፉት ስለ ሀገር ነፃነት ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር ፣ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ሲሉ በሰማዕትነት ያረፉት አቡነ ጴጥሮስ ናቸው ።

እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር ሰኔ ፲፫ ቀን ፴፮ ዓ.ም. አዲስ አበባ የገባው ቺሮ ፓጃሊ "ክረያሬ ዴላሴረ " የተባለው ጋዜጣ ወኪል የሆነውና የምሥራቅ አፍሪካ ዜና መዋዕል አዘጋጅ የነበረው ስለ አቡነ ጴጥሮስ የተሰጠውን ፍርድና የተፈፀመውን ሞት ባየውና በተመለከ



አቡነ ጴጥሮስ በግፍ በተገደሉበት አካባቢ ለመታሰቢያ የቆመላቸው ሐውልት

ተው የሚከተለውን ጽፎ ነበር ።

ሐምሌ ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. አቡነ ጴጥሮስ ተይዘው ወደ ግራዚያኒ ቀረቡ በዚህ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ ግብጻዊው ጳጳስ ቀርበው ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታሰማ በአቡነ ጴጥሮስ ላይ አንዳች ነገር ማድረግ አይገባህም ሲሉ ለግራዚያኒ ነገሩት ምክንያቱም ይላሉ ቄርሎስ አቡነ ጴጥሮስ ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ናቸው በመሠረቱ ሊያዙ ባልተገባ ነበር ከተያዙም ደግሞ ልትገላቸው ትችላለህ ግን በርሳቸው ላይ የምታደርገውን ነገር ሁሉ ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታሰማ ምንም ማድረግ አይገባህም አሉት ።

ይህንንም የተናገሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ድህንነት ሕይወቱን ለመስጠት በሚዘጋጅባት ፣ በዚያች በመከራ ሌሊት ሊይዙትና ሊገድሉት ለመጡት ለሮማውያን ጭፍሮች "ማንን ትፈልጋላችሁ እኔ እንደሆንኩ አለሁላችሁ እነሱን ግን ተውዋቸው ይሂዱ" ሲል በተከታዮቹ ላይ መከራ እንዳይፈጽሙባቸው የተናገረውን ቃል ለሕይወታቸው መመሪያ በማድረግ ፣ መስቀሉንም ተሸክመው በኋላ ለመከተልና ፍኖተ መስቀልንም ተጉዘው የሰማዕትነት አክሊልን ለመቀዳጀት ከበሩ ቆመው ሞትን በሚጠባበቁበት ጊዜ የዛሬ ፶፮ ዓመት ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ነበር ።

አቡነ ቄርሎስ ይህን ማለታቸው በዲፕሎማቲክ ደረጃ ለዓለም ለማሰማትና የአቡነ ጴጥሮስን ሕይወት ለማትረፍ አስበው እንደ ነበር ግልጥ ነው ግን ግራዝያኒ ይህ የአቡነ ጴጥሮስ የሞት ፍርድ እንኳንስ እስከ ግብጽ ከአዲስ አበባ ውጭ እንኳ ከመሰማቱ በፊት በግማሽ ቀን እንዲፈጸም ትእዛዝ አስተላለፈ ።

ጸሐፊው ሲገልጽ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቁመታቸው ዘለግ ፣ ፊታቸው ፈገግ ያለ ፣ መልካቸው ጠየም ያለ አዋቂነታቸውና ትህትናቸው ከገጻቸው የሚነበብ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለብሰውት የነበረው ልብሰ ጵጵስና ጥቁር ካባ ያውም በጭቃ የተበከለ ነበር ። በዚህ ሁኔታ ብፁዕ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ችሎት ቀረቡ ። ለፍርድም የተሰየሙት ዳኞች ሦስት ሲሆኑ እነዚህም ጣሊያናችና የጦር ሹማምንት ናቸው ። የመካከለኛው ዳኛ ኮሎኔል ነበር የቀረበባቸውም ወንጀል ሕዝብ ቀስቅሰዋል ራስዎም አምጸዋል ሌሎችንም እንዲያምጹ አድርገዋል የሚል ነበር ። ዳኛውም ካህናቱም ሆኑ የቤተ ክህነት ባለ ሥልጣኖች ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስም የኢጣልያንን መንግሥት ገዢነት አምነው አማን ብለው ሲቀበሉ እርስዎ ለምን አመጹ ለምን ብቻዎን አፈንጋጭ ሆኑ ሲል ጠየቃቸው ።

አቡነ ጴጥሮስም የሚከተለውን መለሱ "አቡነ ቄርሎስ ግብጻዊ ናቸው ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚያግዳቸው ነገር የለም ። እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ ። ኃላፊነትም ያለብኝ የቤተ ክርስቲያን አባት ነኝ ስለዚህ ስለ ሀገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያኔ እቆረቆራለሁ ከዚህ በቀር ለአናተ ችሎት የማቀርበው ነገር የለኝም ። ለፈጣሪዬ ብቻ የምናገረውን እናገራለሁ እኔን ለመግደል እንደ ወሰናችሁ አውቃለሁ ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ ግን ተከታዮቼን አትንኩ " አሉ

ኢጣሊያዊው ጋዜጠኛ ቺሮ ፖጃሊ እኒህ ጳጳስ ሀቀኛ ነበሩ ነገር ግን ከኢጣ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል

# ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተ ሰብእ

(በከፍያለው መራሂ)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለባሕል ዕድገትና ለኪነ ጥበብ መስፋፋት ሀልውናዋ በኅብረተ ሰብኡ የታሪክ መዝገብ ላይ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድሺ ስድስት መቶዓመታት በላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክታለች። ይህም ይታወቅ ዘንድ ገዳማቱና አድባራቱ የምናኔና የሃይማኖት መካናት ብቻ ሳይሆኑ የሊቃውንት ማፍለቂያና ፡ የጥበብ ምንጭ ሁነው ኑረዋል። በገዳማቱ ውስጥ በተለያዩ ጉባዔያት ሲማሩና ሲመራመሩ የኖሩት መነኮሳት ፡ ቀሳውስትና ሊቃውንት የትምህርትን ፍልስፍና የሚያገናዝቡት ሀሳፊ ከሆነው ከዚህ ዓለም አዱኛ ጋር ብቻ ሳይሆን እውቀትን ወደ ዶኅንነት የምታደርስ የሕይወት ጕዳና አድርገው ያስቧታል በአባቶች ዘይቤ "ካልተማሩ አያውቁ ካላወቁ አይጸድቁ" እንዲሉ በእውቀት አማካኝነት ፍጡር ከፈጣሪው ጋር ይገናኛል ብለው ያስባሉ። "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት" እንደሆነ ተጽፏልና አዋቂ ሰው በመዋዕለ ዘመኑ ፊተናዎችን ሁሉ በትእግሥት ፡ በጥበብና በማስተዋል ያልፋል።

ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጥበብን በማፍለቅና በማዳረስ እንደዚሁም በኅብረተሰቡኡም በጐ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያን የባዕድ መንፈስ ያልተቀየጠበት ንጹሕ ኢትዮጵያዊ የሆነ ባሕልን ጠብቃ ቆይታለች እንደዚሁም ከፍተኛ የታሪክና የፍልስፍና ሀሳበ ፍኖት የሚሰጥ ፡ ለጥናትና ለምርምር እጅግ ጠቃሚ የሆነ የስነ - ጽሑፍ ክምችት አሁን ላለው ትውልድ አበርክታለች። ይህም በሊቃውንት ተመርምሮ እንደተደረሰበት አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የደረሷቸው አያሌ ድርሰቶች እንዳሉ ይነገራል።

ለምሳሌ ቅኔዎች ፡ የዜማ ልክ እንደዚሁም የቅዳሴና የትርጓሜ መጻሕፍት ናቸው። እነዚህም ጽሑፎች በኢትዮጵያውያን አእምሮ የታሰቡ ፡ በዘይቤያቸውና በጥራታቸው ከሌላው ዓለም ያስተሳሰብና የአመለካከት ባሕርይ ጋር ሲነፃፀሩ ፍጹም የኢትዮጵያውያን ሥራዎች የሆኑ ናቸው።

እነዚህም ድርሰቶች ታሪክን ፡ የቆየ ባህልን ፡ የሀገር ፍቅርንና አምልኮተ እግዚአብሔርን ያጠቃልላሉ። ለምሳሌ በጥንቱ የሥልጣኔ ዘመን ዝነኛ ከነበሩት የግሪኩ ሆሜርና የእንግሊዙ ዊልያም ሸክስፔር ጋር በሀገራችን በኢትዮጵያ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የተነሡትን የእነክፍለ ዮሐንስን "ሠም ና ወርቅ" የቅኔ ባሕርይ ስናመዛዝነውና ስናነፃጽረው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አስተሳሰባቸው ይበልጥ የሚያስኝ ረቂቅ ፍልስፍና እንደነበር ከድርሰታቸው ውበት መረዳት ይቻላል። በዜማ ልክ የሄድን እንደሆነ ሀሳባቸው እስካሁን ድረስ የዓለም ሊቃውንት የአእምሮ መለኪያ ነው ተብሎ በሙዚቃ ዓለም የሚነገርላቸው የእነአቶቨንን የሙዚቃ ድርሰት ከኢትዮጵያውያን የዜማ ሊቃውንት ከእነቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ ጋር ስናወዳድረው የኢትዮጵያውያን የፈጠራ ችሎታ ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም።

ነገር ግን ይህን ሁሉ ሥልጣኔ የፈጠረ ችሎታና ሐዲስ ሀሳብ ማፍለቅ ዳር ወጥቶ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ሌላው ዓለም እንዳያውቀውና እንዳይጠቀምበት ለዘመናት በአካባቢ ተጽዕኖ ምክንያት የመገናኛ በሮች መዘጋታቸው አብዛኛውን ጊዜ ከሌላው ዓለም ጋር የነበረን የንግድ ፡ የዲፕሎማቲክና የባህል ግንኙነት ቀዝቃዛ ስለ ነበር ፡ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ለዓለም ያበረከቷቸው አዳዲስ የቅኔ ጕዳናዎች ፡ የዜማ ስልትና ጥበብ በኢትዮጵያ ብቻ ታፍነው ኑረዋል።

እንደሚታወቀው ሁሉ ይህች የምንኖርባት ዓለም በገበያ ትመሰላለች ፡ አንዱ ከሌላው ጋር ሸቀጥን ብቻ ሳይሆን ዕውቀትን አዲስ ሀሳብን ይለዋወጣል። እኛ ኢትዮጵያውያን ከሌላው ዓለም ብዙ የምንቀስመው ጥበብ እንዳለ ሁሉ ሌላውም ዓለም ከእኛ እንዲሁ ትምህርትን ይማራል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አንዱ ከሌላው የማይማር እርሱ ሰነፍ ነው ይላል። ከዚህ ላይ ልብ ብለን ልናስተውለው የሚገባን የኢትዮጵያ ገዳማት የሃይማኖት ኢኒስቲቲዩት ብቻ ሳይሆኑ የፍልስፍና ፡ የእውቀት የቅኔና የሙዚቃ ትምህርት ቤቶች መሆናቸውን ነው። ለምሳሌ የሀሳብ ሰዎች የምንላቸው ቅዱስ ያሬድ ክፍለ ዮሐንስ ፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ወዘተ ... የመሳሰሉት ሊቃውንት የተገኙበት በገዳማቱ ውስጥ ከሚገኙት የጉባዔ ቤቶች(ትምህርት ቤቶች) እንደሆነ አይጠረጠርም።

የሊቃውንቱንም የድርሰት ጠለበረከት በተለያዩ የሙያ መስኮች መሆኑን እናውቃለን። ለምሳሌ ቅዱስ ያሬድ ድጓን ያህል ከፍተኛ ድርሰት ሲደርስ ምሥጢራቱ የተለያዩ ይሁኑ እንጂ የዜማው ስልት በሦስት መሠረታውያን ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው። እነርሱም ግእዝ ፡ እዝልና አራራይ በመባል ይታወቃሉ። እንደዚሁም አብን በግእዝ፣ ወልድን በእዝል ፡ መንፈስ ቅዱስን በአራራይ መስሎ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት አመሥጥሮ ደርሷል። ይህም ድርሰት በሙዚቃ ሊቃውንት ዘንድ እጅግ በጣም ተደናቂነትን አትርፏል። ሊቁ ክፍለ ዮሐንስም በቅኔ ፍልስፍናው ዕለቱን ፡ ዘመኑን ደብሩንና መሪውን በአንዴት "ጉባዔ ቃና" አገናዝቦ እንዲህ ሲል ተቀኝቷል።

"ዮም ዕለተ ብዙኅ ትፍሥሕት እስመ ደብረ ታቦር ቆመ ፈጣሪ ወበደብረ ብርሃን ዳዊት"

ዝነኛው ደራሲ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም የስነ - ፍጥረት ተመራማሪ እንደነበር ሰዓታት በተባለው መጽሐፍ ስለዝናም ሲናገር እንዲህ ይላል። በረቂቅ ጉም ጢስ ውኃን የሚቋጥረው ከትልቅ ባሕር ላይ አውጥቶ የሚያወርደውም ከዚያው ነው ይላል። ሊቁ ስለዝናም፣ ነጐድጓድና መባርቅት ጠባይ በሰፊው ተንትኖ በድርሰቱ ያስረዳል። ሌላው ደግሞ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ የነበሩት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ናቸው። እርሳቸውም በስነጽሑፍ ዝነኛ ከመሆናቸውም በላይ የኅብረተሰብእ ሳይንስ ወይም የፖለቲካ ጥበብ እንደነበራቸው የድርሰታቸው ባሕርይ ያስረዳል።

ለምሳሌ "በቀያፋ ልማድ መስሏችሁ ዝንጋኤ ፡ አደራ እንዳትረሱ ያፍሪካን ትንሣኤ" ይህ የፖለቲካ ቅኔ (ግጥም) የሚያስረዳው በዘመናቸው ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን እንደ ቅርጫ ሥጋ ተከፋፍለው ይዘውት ስለነበር ፡ በነበራቸው አህጉራዊ አመለካከት ጭቆናን ፡ ብዝበዛንና የፍትሕ መጓደልን በማየት፣ እንደዚሁም አፍሪካ በተፈጥሮ ያገኘችውን ነፃነት ከውጭ በመጣ የኃይል ግፊት የነፃነትን ሸማ በመገፈፏ ምን ያህል እንደ እግር እሳት እንዳንገበገባቸው የሚገልጽ ባሕርይ ያለው ሲሆን ፡ መልእክታቸውንም ለአፍሪካ ልጆች በቅኔ ድርሰታቸው አስተላልፈዋል። ይህም ትንቢታዊ የፖለቲካ ቅኔ እንደሚያስረዳው ዛሬ ከጊዜ ወደ ጊዜ አፍሪካውያን የነፃነትን አየር እየተነፈሱ የአፍሪካ ትንሣኤ ጐህ ከቀደደ አያሌ ዓመታት አልፈዋል። አፍሪካውያንም ለአፍሪካ ትንሣኤ በኅብረት ይዘምራሉ።

እንግዲህ በዚህ አንፃር ቤተ ክርስቲያን ለረዥም ዘመናት ትውልዱን በሃይማኖት ፡ በሀገር ፍቅር ፡ በሞራል እያነጸች ለኅብረተሰብኡ መኩሪያ የሆኑ ሊቃውንትን ስታበረክት ኑራለች። በጠቅላላው ቤተ ክርስቲያን በትምህርት ፡ በባሕል ዕድገት በኪነጥበብ መስፋፋት ብዙ ሊቃውንትን በማውጣት አምልኮተእግዚአብሔርን በመስበክ ለኅብረተ ሰብኡ ያበረከተችው አስተዋጽኦ እጅግ ሰፊ ለመሆኑ ታሪክ ምስክር ነው።

---

# በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን...

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ሊያለጋሲዮን ታዞ የመጣው አስተርጓሚ ዳኞች የሚሉትን ብቻ ከማስተርጐም በቀር ጳጳሱ የሚናገሩትን ሐቀኛ ንግግር አላስተረጐመም እኔ እንኳን የሰማሁት በአዲስ አበባ ለሰላሳ ዓመት የኖረው የእቴጌ ሆቴል ሐላፊ የነበረው የግሪክ ዜጋ ማንድራኮስ አጠገቤ ተቀምጦ ስለነበር የተናከገሩትን ሁሉ ስለገለጠልኝ ነው እኔ እንደሰማሁት ፍርዱን ለመስማት በብዛት የተሰበሰቡት ጣልያኖችና ታዞ የወጣው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሐቀኛ የሆነውን ንግግራቸውን ቢሰሙ ኖሮ ልባቸው ይነካ ነበር ይላል።

ሆኖም አስተርጓሚው በጳጳሱ ላይ ተጽዕኖ ስላደረሰባቸው እውነተኛ ንግግራቸው ሳይገለጥ እንደቀረ ይጽፋል። ቀጥሎም ብፁዕነታቸው በፍርድ ችሎት ላይ እንዳሉ ሕዝቡ ሁሉ ስለርሳቸው እያዘነ ሳለ መስቀላቸውን አውጥተው እየጸለዩ ሕዝቡን ባረኩ ወዲያው የሞታቸው ፍርድ ሲሰማ ሕዝቡ በኢጣሊያ የእጅ ሰላምታ አይነት እጁን እንዲያነሣ ታዘዘ በዚያን ጊዜ አቡነ ጴጥሮስ የሞታቸው ሰዓት መድረሱን አውቀው ሰዓታቸውን ከኪሳቸው አውጥተው ተመለከቱ። በዚህ ጊዜ ሁሉ ምንም ፍርሃት አይታይባቸውም ነበር። የሞታቸውን ፍርድ ያነብ የነበረው ኢጣሊያዊ ዳኛ ግን ይንቀጠቀጥ ነበር። ታላቅ ፍርሃትም በፊቱ ላይ ይታይ ነበር።

ይሙት በቃ የተፈረደባቸው ብፁዕ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ በችሎት ፊት ለብዙ ሰዓታት ቆመው ስለዋሉና ደክሞአቸው ስለነበር ለመቀመጥ ፈልገው ዳኛውን በትሕትናና በፈገግታ ጠየቁት እንዲቀመጡም ፈቀደላቸው በመጨረሻ የሞታቸው ፍርድ ከተነበበ በኋላ የፈረዱባቸውን ዳኞች ጸልየው በመስቀላቸው ባረኩዋቸው ብፁዕነታቸው እስከ መቃብር አፋፍ ድረስ የፍርሃትና የድንጋጤ ምልክት ያይደለ ከልብ የሆነ ፍጹም የክብር ትሕትና ይታይባቸው ነበር።

የሀገራቸው በጠላት መወረር ፡ የሕዝባቸው መገደልና መታሰር የቤተ ክርስቲያናቸው መደፈር እስከ ሞት ያደረሳቸው እኒያ እውነተኛ ጳጳስ እንዲገደሉ ሲወሰዱ ጥይት አልፎ ሌላ ሰው እንዳይመታ ግንብ ይፈለግ ጀመር እሩቅ ባለመሄድ ከመካነ ፍትሑ ፲ ሜትር ርቆ ግንብ ያለው መግደያ ቦታ ተገኘና ወደዚያ ተወሰዱ። ከገዳዮቹም አንዱ "ፊትዎን ለመሸፈን ይፈልጋሉን" ሲል ጠየቃቸው "ይህ የአንተ ሥራ ነው" ሲሉ ብፁዕነታቸው መለሱ ከመግደያውም ቦታ እንደደረሱ ወንበር ቀረበላቸውና ፊታቸውን ወደ ግንቡ ጀርባቸውን ወደ ሕዝቡ አድርገው እንዲቀመጡ ሆነ።

ከዚያ በኋላ ስምንት ወታደሮች በስተጀርባቸው ሃያ ርምጃ ርቀው ተንበርክከው በተጠንቀቅ ቆሙ ወዲያው አዛዡ "ተኩስ" በማለት ትዕዛዝ ሲሰጥ ስምንቱም ተኩሰው መቱዋቸው ግንበስምንት ጥይት ሳይሞቱ ቀሩ። መሞታቸውንና አለመሞታቸውን ለማረጋገጥ ዶክተር ተጠራ ዶክተሩም እንዳልሞቱ አረጋገጠ ከዚያም ሌላ ወታደር በሦስት የሽጉጥ ጥይት እራሳቸውን መቶ ገደላቸው።

የብፁዕነታቸውሬሣ ፡ ማንም እንዳይወስደው ባስቸኳይ ከአዲስ አበባ ውጭ ማንም በማያውቀው ቦታ በምሥጢር እንዲቀበር ተደረገ በዚያች ሌሊት በአዲስ አበባ ውስጥ በየቤቱ ልቅሶና ዋይታ ሆነ" ሲል ጽሑፉን ይደመድማል። ይህም ጠላት የሰጠው ምስክርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጀግንነት ሲያረጋግጥ ይኖራል።

በተጨማሪም አቶ ጳውሎስ ኞኞ አቡነ ጴጥሮስ እንዴት ሞቱ ሲል ሙሴ ፓይላክን ጠይቀአቸው እሳቸውም የሚከተለውን ተናግረዋል "አቡነ ጴጥሮስ የተገደሉ ዕለት እዚያው ነበርኩ መጀመሪያ በእጃቸው ይዘውት

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# አራት ዓይናው ዓሣ ሁሉንም ያያል

ሰው ከአንድ ኩሬ ወይም ሐይቅ ውስጥ ሆኖ ለማየት እንደሚሳነው ሁሉ ዓሣም ከውኃ ወጥቶ ለማየት የማይችል መሆኑ ግልጽ ነው ፤ በወንዞች ውስጥ ከሚገኙት የዓሣ ዝርያዎች አናብሌፕስ ወይም በተራ አነጋገር አራት ዓይና የሚባለው ዓሣ ግን ይህንን አስተሳሰብ ውድቅ አድርጎት ይገኛል፡፡ምክንያቱም በውኃና በአየርውስጥየሚገኙትን ምግቦችንና ጠላቶቹን በአንድ ጊዜና ከመቅጽበትም ለይቶ በማየት ለማደን ለመሸሽም ስለሚችል ነው ፡፡

አናብሌፕስ እንደሌሎቹ ዓሣዎች ሁሉ ሁለት ዓይን ብቻ እያለው ለምን አራት ዓይና ተብሎ ተሰየመ? እንዴትስ በአንድ ጊዜ በውኃና በአየር ውስጥ ለማየት ቻለ ? በውኃና በአየር ውስጥ በአንድ ጊዜ የማየቱ ግለትም የዓይኑ አፈጣጠር ምሥጢር እንዲህ ነው ፡፡ ጐረጥ ጐረጥ ያሉና የእንቁላል ቅርጽ ያላቸው ዓይኖቹ የላይና የታች ተብለው የሚጠሩ ሁለት ሁለት ክፍሎች አሏቸው፡፡የታችኛው የዓይኑ ክፍል እንደሌሎቹ ዓሣዎች ዓይን ድብልብል ሲሆን የላይኛው ደግሞ የሰውን ዓይን ይመስላል ፡፡ እያንዳንዱ ክፍልም የሌሎች ፍጥረቶች ለምሳሌ የሰውና የዓሣ አንበሪ ዓይኖች አጥርተው እንደሚያዩላቸው ሁሉ የአናብሌፕስም የዓይን ክፍሎች አጥርተው ያዩለታል ፡፡ ስለዚህም በራሪ ነፍሳትን ወደ ላይ ዘልሎ ለመጉረስ የሚዋኙትንም ወደታች ተወርውሮ ለመጉረስ ይችላል ፡፡ ቢሆንም አብዛኛውን ምግቡን የሚያገኘው ከወንዝ ዳርቻና ጥልቀትም ከሌለው በኩል ስለሆነ የውኃው ሞገድ ገፋፍቶ የሚያመጣለትን ምግብ እስኪያገኝ ድረስ በምግብነቱ ለዓሣው በጣም ተስማሚ የተሟላና ለም የሆነውን ጭቃ ሲጐራርስ ይቆያል ፡፡ በዚህን ጊዜ እንደ ዓሣ አውጭ (አሞራ) ያሉት ጠላቶቹ ዝቅ ብለው ሲበርሩ ካየ ግን ወደ ጥልቁ ውኃ በጭንቅላቱ ተወርውሮ በመግባት ያመልጣል ዓሣ አጥማጆችም መረባቸውን ገና ሲጥሉ ዓይናማው አናብሌፕስ አጥፊውን ቀድሞ ስለሚያይ ቶሎ ብሎ ከዚያ ቦታ ይሸሻል ፡፡ ላይላዩንም ቢዋኝበት ጊዜ የላይኛው የዓይኑ ክፍል በድርቀት እንዳይጎዳበት ጭንቅላቱን ደጋግሞ የሕይወቱ መገናኛና ቤቱ ከሆነው ውኃ ውስጥ በመንከር ዓይኑ እንዲርስና የማየት ኃይሉ እንዲታደስ ያደርጋል ፡፡

የዚህ ዓሣ ዓይን እጅግ ያስገርመን ይሆናል ፡፡ በእውነትም አስገራሚ ነው ፡፡ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ሁሉ በምሳሌ የተነገረ ነው ፡፡ የደቀ መዛሙርቱስ ምርጫ ከትምህርቱ አንዱ ክፍል ይሆን ? አዎ ደካሞችንና የተናቁትን አሣ አጥማጆችም የነበሩትን ሰው አጥማጆች አድርጎ ወደዚህ ዓለም ልኳቸዋልና ማቴ.፬. ፲፰ - ፳፪ ፡፡

በዚህ አንፃር ለሥልጣነ ክህነትም አናብሌፕስ ግሩም ምሳሌ ነው ፤ በሥጋዊ ዓይን ምእመናንን የመገሠጽና የመቆጣጠርን ፤ በዓይን ሕሊና ደግሞ ከአምላክ ጋር ዘወትር እየተገናኙ መማለድን ያመለክታልና ፡፡ ለምን ዓሣ አጥማጆችን መረጠ ? ዓሣ አጥማጆች ዘልቀው ወደ ባሕር በገቡ ቁጥር በሥጋዊ ዓይናቸው ባሕሩንና አየሩን ስለሚማትሩ በዓይነ ሕሊናቸውም የሥራቸውን ፍሬና የአምላካቸውን ቸርነት በመጠባበቅ ፈተናንና ችግርን በማሳለፍ ደግሞም መልካምን ከክፉ በመለየት ብዙ ልምድ ያላቸው በመሆናቸው ነው ፡፡ ማቴ. ፲፫. ፵፯ - ፵፰ ፡፡

የአምላክነቱን ምሥጢር ለአረኞች በቅድሚያ የገለጸ ጌታ አሁንም ልበ ትሑታንን በመፈለግ ዓሣ አጥማጆችን ለሐዋርያት መረጠ ፡፡ ሮሜ ፩ ፡ ፳፪ ፩ ቆሮ. ፩ ፡ ፳፰

በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የቀደሙ አባቶች ካህናትን "ዓዕይንተ እግዚአብሔር" ብለው በፍቅር የሚጠሩዋቸው በከንቱ ሳይሆን ዘርዝር ሁኔታውን ተረድተውት ነው ፡፡ ካህናትም አሜን ብለው የተቀበሉት "አባቴ" መባልን ብቻ በመውደድ ሳይሆን ፍቅሩም የሚያስከትለውን የማስተማሩን የመገሠጹን ከሃይማኖትም ፈቀቅ እንዳይል የመቆጣጠሩን የመናዘዙንና ምሥጢር የመጠበቁን ከባድ ኃላፊነትና መሥዋዕትነትም በመገንዘብ ነው ፡፡ ስለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያናችንን ከሙሉ ፀጋዋና ውበቷ ጥበቧና ዕውቀቷ ሥልጣኗና ተደማጭነቷ ጋር አስረክበው ያለፉት፡፡ተተኪዎቹስ ካህናት ፈለጋቸውን ተከትለዋልን? ሰማያዊው ጥያቄስ ምን ይሆን ? አናብሌፕስ ከተሰኘው ዓሣ ሊማሩት የሚገባ አለን ? አናፕሌፕስ መገኛውና መፈጠሪያው ከሆነ ከውኃ ደጋግሞ ራሱን በመንከር ለላይኛው ዓይኑ ተሐድሶን እንደሚጎናጸፍ ሁሉ ካህናትም ዘወትር ራሳቸውን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም እምነት በማስረከብ ጥበብን ማስተዋልን ጽናትን ቅድስናን ፍቅርን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ሊጎናጸፉና ቤተ ክርስቲያንን በእውነት የክርስቶስ ቤት ሊያሰኟት ይገባል፡፡በዚህ ጊዜ ብቻ ነውና"ዓዕይንተ እግዚአብሔር" ሊባሉ የሚገባቸው ፡፡ ፩ጴጥ. ፪ ፳እና ፱ ራዕይ ፩ ፡ ፮ ፡፡

ከናሽናል ጂኦግራፊክ መጋዚን

ቅጽ 153 ቁጥር 3

እንግዳወርቅ ጥሩነህ



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በሸዋ ሀገረ ስብከት ልማትን ለማስፋፋት የቃለዓዋዲው ደንብ በምዕራፍ ፬ አንቀጽ ፲፰ በሚያዝዘው መሠረት የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅድ አውጥቶአል፡፡

በእቅዱ መሠረት የጎጆ እንዱስትሪዎችን ለማቋቋም የገንዘብ የቁሳቁስ ፤ የዕውቀትና የጉልበት እርዳታዎችን ከየሚመለከታቸው ያሰባስባል ፡፡

ከሁሉ በፊት ግን ካህናቱ በዚህ ሙያ ላይ ለመሠማራት እንዲችሉ በትምህርት ያንጻል ስለገንዘብ አስተዋጽኦም በየወረዳው የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ልዩነት የማይታይበት የአንድነት ትብብር እንዲኖር ያደርጋል ፡፡

ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ጠይቀን እንደ ተረዳነው የጎጆ እንዱስትሪን ለማቋቋም ገንዘብ እንደማስፈለጉ ሁሉ ገንዘብና ቁሳቁስ ከምእመናንና ከክርስቲያናዊ ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሚፈለገውን አሰባስቦአል ፤ እያሰባሰበም ነው፡፡

የዕውቀት ፣ የገንዘብ ፣ የቁሳቁስና ሌላውም ተፈላጊ ነገር ሲሟላለት በእቅዱ መሠረት የጐጆ እንዱስትሪዎችን እያቋቋመም ነው ፡፡

እኛም ይህንን መነሻ በማድረግ በአቃቂ በሰቃ የተቋቋመውን የጎጆ እንዱስትሪ ተመልክተናል በዚህም ክፍል ሊቀ ካህናት ጥበቡ አስረስን አነጋግረናል ፤ እሳቸው ስለጐጆው እንዱስትሪ እንዲህ በማለት ያብራራሉ ፡፡

በመጀመሪያ በአቃቂ ወረዳ ፲፱ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ በነዚህም አብያተ ክርስቲያናት በግምባር የሚያገለግሉ ፪፻፹ ካህናት አሉ ፡፡

የጐጆ እንዱስትሪውን ለማቋቋም የሸዋ ሀገረስብከት ሊቀጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሀ/ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገብረ ሕይወት በሚያደርጉት ጥረትና ባወጡት የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅድ መሠረት በወረዳው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በነፍስ ወከፍ ብር ፻ (አንድ መቶ ብር) በማዋጣት ሥራው ሲጀመር ችሎአል ፡፡

አንድ የጎጆ እንዱስትሪ ለማቋቋም በቂ ገንዘብ ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑም በሀገረ ስብከቱ እቅድ መሠረት ከ፲፰ቱ አብያተ ክርስቲያናት ብር አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር

፪. ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አንድ ሺ ብር

፫ኛ. ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ሁለት ሺ ብር


፬ኛ. ከክርስቲያናዊ ተራድኦ ድርጅት


፩/ ቦንዳ ድር

፩/ ቦንዳ ሱፍ

የሹራብና የሸሚዝ ጨርቃ ጨርቅ መሥሪያ ማሽኖች ፫

አግኝተን ሥራውን ጀምረን አጥጋቢ ውጤት እያገኘን ነው እንዱስትሪው ምንና ምን እንደሚያመርት ስንት ሠራተኞች እንዳሉ ሲያብራሩ ደግሞ ፤





የአቃቂ በሴቃ ካህናት በተግባረእድ ላይ እንዳሉ

ይህ በአቃቂ መድኃኔዓለም የተጀመረው የጎጆ እንዱስትሪ የሚያመርተው በሸመና ሥራ ጋቢ ነጠላ ቀሚስ ጥበብ ጃኖ እና ጥንግ ድርብ ከቃጫ ሥራ የወለል ምንጣፍ ዘንቢልና ቦርሳ ከሹራብ ሥራ የአልጋ ልብስ ፡ የአዋቂዎችና የሕፃናት ሹራብ በማሽን ከሚሠሩ ጨርቃ ጨርቆች የኩትና የሸሚዝ ጨርቆችም ገና በመሠራት ላይ ናቸው ፡፡

በሥራ የተሠማሩ ሠራተኞችም ፬ ሲሆኑ እነዚህም ካህናቱና የካህናቱ ቤተሰቦች በመሆናቸው ከዚህ በፊት በካህናት ቤት ይታይ የነበረው የደመወዝ እጥረት በዚህ ሥራ እየተጠናከረና እያደገ በመሔዱ ሥራው በደስታና በስሜት ይካሔዳል ፡፡

ለ፬ ሠራተኞች በየወሩ ሁለት ሺ ሶስት መቶ ብር ደመወዝ ይከፈላል ይህም ገቢ ከምርታችን ውጤት የተገኘ በመሆኑ "ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋል" የሚለውን አምላካዊ መመሪያ በሥራ እየተረጐምን እንገኛለን ፡፡ ሥራው በ፪ አሰልጣኞች ሲመራ ምርታችንን በይበልጥ ለማጠናከር በጉፋ ማሰልጠኛ ካህናትን እያሰለጠን እና ከዚህም የሚገኙት በይበልጥ ለኃላፊነት እየተዘጋጁ ናቸው ፡፡

ሥራው የተጀመረው በሰኔ ወር ፲፱፻፸፱ዓ.ም.ሲሆን ለደመወዝ ለቆሳቁስ ለሥራ ማካሔጃ ወጭ አድርጐ ከወጭ ቀሪ ዛሬ በእንዱስትሪው ስም በባንክ ሰባት ሺህ ብር ተቀማጭ ሊኖረው ችሎአል ፡፡

ሊቀ ካህናት ጥበቡ ለማጠቃለል ሲያብራሩ ሥራው ባጭሩ በዚህ ብቻ የሚቆም አይደለም የቆዳ ጫማ ከእንጨት የሚሠሩ የቤት ዕቃዎች ሶፋ ፤ ቁምሳጥን ወምበርና ጠረጴዛዎችም እንደሚሠሩ እቅዳችን ነው በዚህ አጋጣሚ በሥራው ስለቾን ደከመን ሳይሉ ከሚሠሩ ታታሪዎች መምሬ ሥዩም ዳኜን ቁስ ለማ መኩሪያን አባ ምሕረቱ ፈለቀን መሪጌታ ቀጸላ ኃይሌን የቀሩትን ሁሉ ሳመሰግን በበለጠ ትጋት የበለጠ ምርት አምርተን ምሳሌነታችን ለሌሎች እንዲዳረስ በርቱ እላለሁ ብለዋል ፡፡

ተከታዩን በ፲፩ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

## ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ዚህም ምናልባት የሚቀርበው መልስ አማርኛው በሚገባ ተጠብቆ ካልተላለፈ በዘፈቀደ ይሆንና ምሥጢሩ መስመሩን ለቅቆ ልዩነት ይፈጠራል የሚል መልስ ሳይሆን አይቀርም ይኸንንም ከተረዳን በኋላ ያለፈው አልፏልና ለዛሬውና ለወደፊቱ እስኪ አስተያየት እና ቅርብ ለአንድ ዓይነት ንባብ ወይም ዓረፍተ ነገር በአንድምታ የሚተላለፈው ትርጉም መሠረታዊ አሳቡን አይዘልም ወይ? የማይዘልስ ቢሆን ያልተነበበውን መተርጐም ይገባል የሚለውን ፍርድ ያስገኛል ወይ? አንድ መጽሐፍ እንዲያነብ የተሰጠው ሰው መጽሐፉ በውስጡ ያዘለውን ፍሬ ነገር በሚያውቀው ቋንቋ በራሱ የአገላለጽ ስልት እንዲያስረዳ ከመጠየቁ በቀር አማርኛውን ሙሉ በሙሉ አጥንቶና የወረቀቱን በአንጕሉ ላይ ጽፎ መልሱን ያበረክታል ወይ?

ይህ ሁሉ በዝርዝር ሲመለከቱት ሲወያዩበት አስቸጋሪ ነው በመሆኑም ሊቃውንቱ፣

፩. ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራምና ለወደፊቱ ሊቃውንት ጽሕፈት የመጻፍና የሥነ ጽሑፍን ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ መጻሕፍቱ በመሠረቱ የተመለሱባቸውን ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የማጥናት ልምድ እንዲያውም ግዴታ ቢኖርባቸው፤

፪. የመጻሕፍቱ ምሥጢር ከታወቀ በዘመኑ አማርኛ ትርጉሙ የሚካሔድበትን ሁናቴ የዘመናችን ሊቃውንት ቢቀይሱና ንጉሡ ዳዊት ከቤተልሔም ምንጭ ውሃ እንዲጠጣ መፈለጉን አስመልክቶ ብዙዎች የታወቁ የኢትዮጵያ ምንጮች እያሉ እንደልደታ ወሃ ማየ ሕይወትነት ያለው ነው የተባለው፤ እንዲሁም በየዘመኑ የተነሡ የነገሥታት ባለሟሎች እያሉ በቅዳሴ ማርያም ትርጉም እንደ ጥቁር ከብቱ እንደቆብ አስጥል ኃይሉ ያሉትና የመሳሰሉት መጠቀሳቸው ቢቀርና ያልተነበበ እንዳይተረጐም ቢደረግ በጠቅላላውም ይኸንንና

ይኸንን የመሳሰለው ሁሉ የጊዜውን የሥልጣኔ ዕድገት እየተከተለ ቢሻሻል መልካም ነው ።

"ባለህ እርጋ" የሚለው የአሳበ ግትሮች ፍልስፍና የምርምር ሰዎች በሆኑት ሊቃውንት ዘንድ ቦታ ሊኖረው አይገባምና ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

## በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ

ከገጽ ፲፱ የዞረ

የነበረውን መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ተሳለሙት ቀጥለውም የያዙትን መስቀል አማትበው ሕዝቡን ባረኩ የኪሳቸውንም ሰዓት አውጥተው ካዩ በኋላ መልሰው ከኪሳቸው ከተቱት ወዲያው ወታደሮች በሩምታ ተኩሰው ገደሉዋቸው ይህ እንደሆነ አስገዳዩ ኰሎኔል ተመልካቹን ሕዝብ አጨብጭቡ ብሎ አዘዘና ተጨበጨበ ።

ማታ ከአስገዳዩ ኰሎኔል ጋር ተገናኝተን ስንጫወት በዚህ ቄስ መገደል እኮ ሕዝቡ ተደስቷል አለኝ እንዴት ብለው አላየህም ሲያጨበጭብ አለኝ እኔም ባታውቀው ነው እንጂ የሕዝቡ ባህል ሲናደድም ያጨበጭባል አልኩት እንዴት ቢለኝ እጄን እያጨበጨብኩ አሳየሁት እሱም አሳየኝ ከዚህ በኋላ የሆነው ቢሆን እኔ ትልቅ ማስታወሻ አግኝቻለሁ ብሎ አቡነ ጴጥሮስ ሲገደሉ ይዘውት የነበረውን መስቀልና መጽሐፍ ቅዱስ የኪስ ሰዓታቸውን ጭምር አሳየኝ መጽሐፍ ቅዱሱ መሐል ለመሐል በጥይት ተሰንጥቋል መስቀሉም ልክ በመሐከሉ ላይ ጥይት በስቶት ወጥቶአል የኪስ ሰዓታቸውንም እንዳየሁት እንደዚሁ ጥይት በስቶታል" ብለው ያዩትን መስክረዋል ።

የአቡነ ጴጥሮስ አሟሟት ይህን የመሰለ ነው እኚህ ታላቅ አባት በዕውቀትና በትምህርት ችሎታ የእግዚአብሔር ፀጋ የመንፈስ ቅዱስ ሃይል የተሰጣቸው ስለነበሩ ስለ እውነት ስለ ክርስቶስ ፍቅር ስለ ሰላም ስለ እኩልነት ስለፍትሕ በሕይወተ ሥጋ ሣሉም ቢሆን ታላቅ ተጋድሎ ያደርጉ ነበር ። ይህን እያደረጉ ያለፉ አባቶች ሁሉ በቤተክርስቲያን ትውፊታዊ ታሪክ ወርቃዊ ስጦታ ተአምራዊ ይባላል ።


እርግጥም እውነተኛ ፍትሕ ነፃነት በጠፋበት በዚያን ዘመን አቡነ ጴጥሮስ ስለ እውነት ስለ ፍርድ ስለ ሰላም በፋሽስት ፊት መስክረው መሞታቸው እርግጥም ተአምር ነው ስለዚህ ሞታቸው ብዙ አርበኞችን ቀሰቀሰ ደማቸውም የነፃነትን ፍሬ አፈራ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም አቡነ ጴጥሮስ ያረፉበትን ሐምሌ ፳፪ ቀን በየዓመቱ በጸሎት ታስባቸዋለች ።

ስለዚህ ሥራ የሰሩ ሰማዕታት በታሪክ ማህደር የሚኖራቸው ቦታ ከሁሉ የላቀ በመሆኑ አቡነ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ያረፉት ይህንን አርአያ በመከተል ነው ። እንዲህ ያሉትም መንፈሳውያን አባቶች ቢኖሩም ቢሞቱም ታሪካቸው ሕያው ሆኖ ከመኖሩ ሌላ ለስማቸውም አዲስ ምዕራፍ ስለሚከፍትለት ትውልድ ሁሉ ሲያስባቸው ይኖራል ። ስለ ሀገርና ስለ ቤተ ክርስቲያን ውድ ሕይወታቸውን ሰጥተዋልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# ክርስቲያናዊ ጋብቻ



ዲያቆን በላይ ተገኝና ወ/ት ገነት ደበበ ከቁርባን በኋላ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ

ክርስቲያናዊ ጋብቻ ለሰው ልጅ የመጀመሪያው ፍጹም ደስታ ነው ።

እግዚአብሔር አምላካችን ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ክብሩ ብቻውን እንዳይቀር ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር አለ። በመጀመሪያም አዳምን ፈጠረ ። አዳምም ብቻውን እንደሆነ አውቆ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለምና ለአዳም ሴትን እንፍጠርለት ካለ በኋላ ከሌላ መፍጠር ሳይሳነው አንድነታቸውን ለመግለጽ ከአዳም የጐን አጥንት አንዲቱን በማውጣት ሔዋንን ፈጠረለት ከዚያም ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉአት አለ ። እግዚአብሔርም የፈጠረውን ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ ።እንደዚህም አድርጎ የፈጠረውን ጋብቻ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ"ዘፍ፪፣፳፬፣ማቴ . ፲፱፣፭ ። ባልና ሚስት አንድ አካል ከሆኑበት ቀን ጀምሮ መለያየት አይፈቀድላቸውም እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለይ አይችልምና ። ማር. ፪ ፲፱ ። እንዲሁም ማንም የልጅነት ሚስቱን አይፍታ ትንቢተ ሚልክ፪፣፲፬-፲፮

ስለዚህ በእነዚህ ሁለት የመጀመሪያ ሰዎች ምክንያት ዓለም ዛሬ በሕዝብ ተመልታ ትታያለች ።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የመጀመሪያ ተአምሩን በሠርግ ቤት በፈጸመ ጊዜ የጋብቻን ታላቅነት እንደገለጸው አባቶች በብዙ መንገድ ይተነትናሉ ። በዓለም የነበሩና ያለፉ ሊቃውንትም ስለጋብቻ ታላቅነትና ክቡርነት ባላቸው የዕውቀት መጠን ያህል ገልፀውታል ።

ለምሳሌ፡- ጋብቻ የዓለም እናት ናት ። ከተሞችንና ቤተክርስቲያንን ትመላለች ለመንግሥተ ሰማያትም ዜጎችን ታዘጋጃለች ሲሉ አንድ ሊቅ ተናግረዋል ።

ነቢዩ ሰሎሞንም፡- ባለሙያና ኃይማኖተኛ የሆነች እርጋታ ያላት የባሏን ንብረት ሕይወትና ደህንነት ጥበቃ በሰላም የምትኖር ሚስት ከእግዚአብሔር እጅ ብቻ የምትገኝ ምርጥ ስጦታ ናት" ብለዋል ። ይህ አነጋገር ለሴቷ ብቻ የሚገለጽ ቢመስልም ሁለትነት በጋብቻ ውስጥ ሲጠቃለል እኔ፤ ለእኔ የሚለውን ሰርዞ እኛ ለእኛ በሚለው ቃል ይተካልና እንዲያውም በደፈናው የጋብቻን ክብር የሚገልጽ ሆኖ ይገኛል ።

እግዚአብሔር ለሰው እንደሚያስፈልግ አውቆ የፈጠረውንና ክርስቶስ የመጀመሪያ ተአምሩን የገለጸበትን ጋብቻ ሰው ዝቅ ዝቅ ሊያደርገው ወይም ባልተስተካከለ የጋብቻ አመሠራረት ምክንያት ሊነቅፈውና ሊያስነቅፈው አይገባም ። እግዚአብሔር የፈጠረውንሁሉ ከምስጋና ጋር ቢቀበሉት መልካም ነውና ።

ስለዚህም ጋብቻ ለእኔም ይድረሰኝ ከማን አንሸ ወይም ለሙከራ ያህል የሚገባበት በተለይም ፍትወተ ሥጋን ለማሸነፍ ያህል ብቻ የሚደረግ ከሆነ ትክክለኛው የጋብቻ አመሠራረት አይደለምና ውጤት አልባም ስለሚሆን ቢቀርም አይጐዳ ።

የህብረተሰብ ምንጭ ና የማህበራዊ ኑሮ መለኪያ የሆነው ጋብቻ ባልባሌ ሰዎችና የተከበረውን በሚያዋርዱ ምክንያት የኑሮ እንቅፋትነታቸውና የሚያስከትለውም ጉዳት ለብዙ ቤተሰብ የኑሮ መጓደል ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን ። በአንጻሩም መልካም ጋብቻ የሚያበረክተው ድርሻ ከዓለም አልፎ እስከ መንግሥተ ሰማያት ያደርሳል ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአለፉት ደጋግ ሰዎች መካከል ጥቂቶቹን እንኳ ብንጠቅስ አብርሃምና ሣራ ይስሐቅና ርብቃ በሌላው ሁሉ ከሰሩት መልካም ሥራቸው ጋር በጋብቻም ያስገኙት ውጤት ተደምሮ ለመልካም ጋብቻ ምሳሌነት ሲጠቀሱ ይኖራሉ ።

ለዚህም ሁሉ የሚያበቃው አመሠራረት በፍቃደኝነት የሆነ እንደሆነ ነው መሠረቱ መልካም የሆነን ነገር ሁሉ ምንም ነገር ሊያነዋውጸው አይችልም ። ለምሳሌ ቤት ሲሰራ ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ተቆፍሮለት በድንጋይና በስሚን



www.ethiopianorthodox.org

ቶ ታንጾ ካስፈለገም በብረት ታስሮ ቢሰራ ከላይ የተጣለው ቤት ከነመሠረቱ ነፋስም ሆነ ጐርፍ አይገፋውም ። እንዲሁም ሁሉ ለጋብቻ ኃይልና ጽንዕ የሚሆነው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው ይኸንንም ቅድስት ቤተክርስቲያናችን በትምህርትዋ ሁሉ አስፋፍታ በመግለጽ ለምዕመናን ታስተምራለች ።

ይኸን በማክበር ጋብቻቸውን የሚመሠርቱ ሁሉ በአካሄዳቸውና በአኗኗራቸው የሚያሳልፉት ኑሮ በረከት የመላበት መሆኑ እሙን ነው ።

በዚሁም መሠረት የቤተክርስቲያናችንን ሕግና ሥርዓት በመከተል ዲያቆን በላይ ተገኝና ወ/ት ገነት ደበበ ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጋብቻቸውን ፈጽመዋል ። ሁለቱ ወጣቶች በካቴድራሉ ተገኝተው ጋብቻቸውን በፈጸሙበት ወቅት የቤተ ክርስቲያኑ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ የቀድሞ ዲያቆናት ማህበርና የማህበረ ክርስቶስ መዘምራን ለሙሽሮቹ ክብር ልዩ ልዩ መዝሙሮችን በማቅረብ ደስታቸውን ገልፀውላቸዋል ።

በዚህ አጋጣሚም ሁለቱን ሙሽሮች ለማስተዋወቅ ቢያስፈልግ ዲያቆን በላይ ተገኝ አስቀድመው በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በዲቁና በማገልገል ላይ እያሉ ዘመናዊ ትምህርታቸውንም በመከታተል ከፈጸሙ በኋላ ይኸው ቅን መንፈሳዊ አገልግሎታቸውና ትጋታቸው ታይቶ በካቴድራሉ አማካኝነት ለከፍተኛ ትምህርት ወደሮማንያ ተልከው ለአምስት ዓመታት ያህል የቲዎሎጂ ትምህርታቸውን ፈጽመው ተመልሰዋል ።

አሁንም ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ የሚገኙ ቅንና ትሁት መንፈሳዊ ወጣት ናቸው ዲያቆን በላይ ተገኝ በዲቁና አገልግሎት ላይ እያሉ "ማህበረ ሥላሴ" በመባል ይታወቅ በነበረ የመንፈሳውያን ወጣቶች ማህበር በልዩ ልዩ ሥራዎች ለብዙ ጊዜ ያገለገሉ ከመሆናቸው ሌላ በተለያዩ መንፈሳውያን ማህበራትም እየተዘዋወሩ በማስተማር መንፈሳዊ ድርሻቸውን አበርክተዋል ።ይህም ለቅንነታቸውና ለመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ቋሚ ምስክር ነው ።እሁንም ይህን መንፈሳዊ ሕይወት ባሉበት ዓለም ውስጥ ሆነው ለመተርጐም እራሳቸውን በመግዛትና በመጠበቅ ከቆዩ በኋላ ጋብቻቸውን ከወ/ት ገነት ደበበ ጋር በተክሊልና በቁርባን ለመፈጸም በቅተዋል ። አበው ሲናገሩ "ባልና ሚስት ከአንድ ባህር ይቀዳሉ" እንዲሉ ወ/ት ገነት ባላት መንፈሳዊ ሕይወትና ቅንነት ከእርሳቸው ተለይታ የማትታይ በመሆንዋ ለዚህ የተቀደሰ ጋብቻ ብቁ ሆናመቅረቧ /መገኘቷ/ ይህን ዓላማ ለሚከተሉ ሁሉ መልካም አርአያነት ነው ። ሁለቱ ወጣቶች ባላቸው መንፈሳዊ ሕይወት በመስማማት የፈጸሙት ይህ ቅዱስ ጋብቻ ፍሬው መልካም መሆኑ አያጠራጥርም ። የመሠረቱት አዲሱ የሕይወት ምዕራፍ በቅዱስ ጋብቻ የከበረ መሆኑ ሥጋው ደሙን ሲቀበሉ ተፈጽሟልና ነው ።

ከላይ እንደተገለጸው ዲያቆን በላይ ተገኝ በካቴድራሉ አገልጋይ በነበሩበት ጊዜና አሁንም ስላላቸው መንፈሳዊነትና ቅንነት መታሰቢያ እንዲሆን የቀድሞ ዲያቆናት ማኅበር ባዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት የቤተ ክርስቲያኑ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ት/ቤት ቅጽር ገቢ ለሙሽሮቹና ለአጃቢዎቻቸው የብስኩትና የፍራፍሬ እንዲሁም የለስላሳ መጠጥ ግብዣ በማድረግ ሸኝተዋቸዋል ። ከዚያም በኋላ ሙሽራውና ሙሽራይቱ በመጡበት አኳኋን ታጅበው ወደቀኑ ዝግጅታቸው አምርተዋል ።

እኛም ሙሽሮቹ የመሠረቱት አዲሱ የሕይወት ምዕራፍ በዘመናቸው ሁሉ መልካም እንዲሆንላቸው የልጆቻቸውንም በጐ ነገር ለማየት እንዲያበቃቸው እንመኝላቸዋለን ።

ወ/ት ንብረት አበበ

## አይዞአችሁ አትፍሩ

ከገጽ ፮ የዞረ

ልቁ ችግር ከልብ የመነጨውን እምነት ይዞ እግዚአብሔርን አለመከተልን ካለማመን ፍርሃትና ጭንቀት የሚያስከትል መሆኑ ከላይ ተገልጾአል ።

ቢሆንም በሰው ልጅ የነበረው ሞት አስጨናቂነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው ጸዋትወ መከራና ባደረገው መስዋዕት ተወግዶልናል ለምሳሌ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ (እፈቱሰ እፍልስ ወእትፈአጥ እም ዝንቱ ዓለም) ከክርስቶስ ጋር እኖር ዘንድ ከዚህ ዓለም መለየትን እናፍቃለሁ ያለው ቃል በእውነተኞች ክርስቲያኖች ዘንድ ሞተ ሥጋ የማያስፈራ መሆኑን ያመለክታል በሌላም በኩል ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚሁ ሲናገር ባንተ ያለውን ግብዝነት የሌለበትን እምነትህን አስባለሁ ይህም እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበረባቸው ባንተም ደግሞ እንዳለ ተረድቻለሁ ሲል የእምነቱን መሠረተ ዓላማ ከገለጸ በኋላ ወደ ማስተማር በሚሰማራበት ጊዜ ፍርሃት እንዳያድርበት ሲያበረታታው እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጅዎቼን በመጫኔ ባንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ ፤ እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ፤ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃትን መንፈስ አልሰጠንምና ብሏል ። ፪ኛ ጢሞ.፩፥፭-፯

ከንፈርግብ ማርቆስ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቁ. 116616
የመል. ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org